# የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያ

# የወላጅ መብቶች ለልዩ ትምህርት K-21

የተማሪ እድሎችን ማሻሻል ቢሮ
**255 Capitol Street NE**
**Salem, Oregon 97310**

ይህ ሰነድ ከ U.S. የትምህርት ክፍል ሞዴል የስርዓት ጥበቃዎች ማስታወቂያ (ሰኔ 2009 ዓ.ም)  ጋር የሚስማማ ሲሆንእንደ አስፈላጊነቱ፡ የኦሪገን ህጎችን በተመለከተ የተለየ መረጃ አለው።

ይህ ሰነድ እየተዘጋጀ ያለው ለ 2020-2021 የትምህርት ዘመን ነው። ነገር ግን የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ከዚህ የተለየ ሌላ ማስታወቂያ እስካልተሰጡ ድረስ ይህ ሰነድ ተፈጻሚ ይሆናል።

ይህንን ሰነድ በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች ወደ የሚቀጥለው ማድረስ ይቻላል፡-


የተማሪ እድሎችን ማሻሻል ቢሮ

(Office of Enhancing Student Opportunities)

የኦሬገን የትምህርት ክፍል

255 Capitol Street

Salem, OR 97310

(503) 947-5634


ይህ ሰነድ በአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ድህረ ገጽ ላይ በኤሌክትሮኒክ መልኩ ይገኛል፡-

https://www.oregon.gov/ode/rules-and-policies/Pages/Procedural-Safeguards.aspx

የስቴት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ እና የኦሪገን የትምህርት ክፍል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር ማንነት፣ በዕድሜ ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ምንም ዓይነት አድልዎ ወይም ትንኮሳ እንደማይኖር በማረጋገጥ መስራት ነው። ሁሉም እኩል የሆነ እድል ስለማግኘት እና አድሎአዊ አለመሆን በተመለከተ ጥያቄዎች ያላቸው ሰዎች በኦሪገን የትምህርት መመርያ ክፍል 255 Capitol Street NE, Salem, Oregon 97310 ያለው የስቴት የሕዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪን በስልክ ቁጥር 503-947-5634፤ ፋክስ 503-378-5156 ማነጋገር አለባቸው።

በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ያለው መረጃ፡-

- በ 34 CFR 300.30 ላይ እንደተገለጸው፣ በአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ህግ (Individuals with Disabilities Education Act) (IDEA) መሰረት ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ የሆኑ፣ ወይም ለሚሆኑ፣ የልጆች ወላጆች ነው።

- ከ ORS 419B.550 እስከ 419B.558 እንዲሁም በ OAR 581-015-2325 መሰረት አካል ጉዳተኛ ለሆኑ አዋቂ ተማሪዎች ወይም ነጻ ለወጡ ልጆች ነው።

**የ "ወላጅ" ትርጉም**

IDEA ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ወላጆች የተወሰኑ መብቶችን ይሰጣል። ወላጅ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፡-

- የአንድ ልጅ ወላጅ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ፤
- የአንድ ልጅ የማደጎ ወላጅ፤
- ህጋዊ አሳዳጊ (ከስቴት ድርጅት ሌላ) ወይም ለልጁ ደህንነት ህጋዊ ሃላፊነት ያለበት ሌላ ሰው፤
- በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ወላጅ (አያት፣ የእንጀራ ወላጅ፣ ወይም ሌላ ዘመድን ጨምሮ) ምትክ ከልጁ ጋር አብሮ የሚኖር እንደ ወላጅ የሚሆን ግለሰብ፤ ወይም
- በትምህርት ቤቱ ወረዳ ወይም በወጣቶች ፍርድ ቤት የተሾመ ምትክ ወላጅ።

እንደ ወላጅ ለመሆን ከአንድ በላይ ሰው ብቁ ከሆነ፣ እና ወላጅ ወይም የማደጎ ወላጅ እንደ ወላጅ ለመሆን እየሞከሩ ከሆነ፣ ወላጅ ወይም የማደጎ ወላጅ በ IDEA መሰረት ወላጅ እንደሆኑ ይገመታል። ሆኖም፡-

- ወላጅ ወይም የማደጎ ወላጅ ለልጁ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለማድረግ ህጋዊ ስልጣን ከሌለው ይህ ህግ አይተገበርም።
- እንደ አንድ ልጅ ወላጅ ሊሆኑ የሚችሉ ወይም ልጁን ወክለው ትምህርታዊ ውሳኔዎችን የሚወስኑ የተወሰነ ሰው(ዎችን) የሚለይ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም የፍርድ ድንጋጌ ካለ ያ ሰው ለልዩ ትምህርት አላማዎች ወላጅ ይሆናል።

እድሜያቸው 18 አመት የሞላቸው ተማሪዎች፣ ያገቡ የሚመለከታቸው ወጣት ተማሪዎች፣ ወይም በህግ ነጻ የወጡ፣ እና በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠ አሳዳጊ ያላቸው፣ ስለራሳቸው ትምህርት ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው። እንደዚህ አይነት ተማሪዎች በዚህ ህትመት ላይ የተገለጹት ሁሉም የ IDEA የወላጅ መብቶች ይኖራቸዋል።

ይህ ምልክት ለአዋቂ ተማሪዎች እና/ወይም ለአካለ መጠን ሳይደርሱ ነጻ ለወጡ ልጆች ተግባራዊ የሚሆነውን ማስረጃዎችን ያመለክታል።

በዚህ መጽሃፍ ውስጥ ያሉት ለአንድ ልጅ ተፈጻሚ የሚሆኑት መብቶች በ IDEA ስር ብቁ ለሆነ አዋቂ ተማሪ ላይም ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ያስተውሉ።

ሁሉም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በ IDEA መሰረት ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ አይደሉም። አንዳንድ ተማሪዎች ዋና ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የአካል ጉዳቶች ሊኖርባቸው ይቻላል ነገር ግን በ IDEA ስር ለአንዱ የአካል ጉዳት ምድቦች የብቁነት መስፈርቶችን አያሟሉም። እነዚህ ልጆች እንደ የ1973 የመልሶ መቋቋም ህግ ክፍል 504 ወይም የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ህግ (ADA) ባሉ፣ በተለያዩ የፌደራል ህጎች ሊጠበቁ ይችላሉ። የእነዚህ ልጆች እና የወላጆቻቸው መብቶች ተመሳሳይ ናቸው፣ ነገር ግን በዚህ መጽሃፍ ውስጥ እንደተገለጹት የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች፣ አንድ አይነት አይደሉም። ስለ እነዚህ ህጎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎን የክፍል 504 አስተባባሪ ያነጋግሩ ወይም በ ODE የሲቪል መብቶች ድረገጽ ላይ ያለውን መረጃ ይመልከቱ።

-

## ማውጫዎች


የ"ወላጅ" ትርጉም .......... 2
አጠቃላይ መረጃ .......... 5
ቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ .......... 5
የአፍ መፍቻ ቋንቋ .......... 6
በሌክትሮኒክስ የሚላክ መልእክት .......... 6
ስምምነት - ማብራርያ .......... 7
ስምምነት .......... 7
ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች (IEE) .......... 10
የመረጃ ምስጢራዊነት .......... 12
ሚስጥራዊነት .......... 12
ማብራርያዎች .......... 12
በግል ሊታወቅ የሚቻል .......... 12
ማስታወቂያ ለወላጆች .......... 12
የመዳረሻ መብቶች .......... 13
የመዳረሻ መዝገብ .......... 14
ከአንድ በላይ ልጆች የሚያመለከቱ መዛግብት .......... 14
የመረጃ ዓይነቶች እና ቦታዎች ዝርዝር .......... 14
ክፍያዎች .......... 14
መዝገቦችን ለማሻሻል የሚቀርቡ ጥያቄዎች .......... 14
ስለ ትምህርታዊ መዝገቦች የመስማት እድል እና ሂደቶች .......... 15
ስለ ትምህርት መዛግብት የችሎት ሂደት ውጤቶች .......... 15
በግል ሊታወቅ የሚችል መረጃን ይፋ የማድረግ ስምምነት .......... 15
ጥበቃዎች .......... 16
መረጃን ማጥፋት .......... 16
አለመግባባቶችን መፍታት .......... 16
ሽምግልና .......... 16
በተገቢ የችሎት ሂደት እና በስቴት የቅሬታ ሂደቶች መካከል ያለው ልዩነት .......... 17
የግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶች .......... 18
የግዛት ቅሬታ ማቅረብ .......... 20
ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማቅረብ .......... 21
የሞዴል ቅጾች .......... 23
ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት በመጠባበቅ ላይ እያለ የልጁ ምደባ .......... 23
የመፍትሄ ሂደት .......... 24
ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት .......... 26
የችሎት ሂደት መብቶች .......... 27
የችሎት ሂደት ውሳኔ .......... 27
የችሎት ሂደት ቅደም ተከተሎች እና አመቺነት .......... 28
የምዝገባ ጊዜን ያካተተ፣ የሲቪል ህግ እርምጃዎች .......... 29
የጠበቃ ክፍያዎች .......... 30
አካል ጉዳተኛ ልጆች በሚቀጡበት ጊዜ የሚኖሩ የአሰራር ሂደቶች .......... 32

የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን......32
አገልግሎቶች......32
የመገለጥ ውሳኔ......33
በማባረር ቅጣት ምክንያት ምደባ መቀየር......35
የክስተት ቦታ ውሳኔ......35
ይግባኝ ......35
ይግባኝ በሚሉበት ጊዜ ምደባ......36
ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እስከ አሁን ብቁ ላልሆኑ ልጆች የሚደረግ ጥበቃዎች......36
በህግ አስከባሪ እና የፍትህ ባለስልጣኖች የሚደረግ ሪፈራል እና እርምጃ......38
በህዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ልጆች ወላጆች በአንድ ወገን ምደባ ለማግኘት የሚያስፈልጓቸው መስፈርቶች......39

## አጠቃላይ መረጃ

የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ትምህርት በሚመለከት የፌደራል ህግ የሆነው፣ የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ ትምህርት ህግ (IDEA)፣ ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳት ላለበትን ልጅ ወላጆች በIDEA እና የU.S. የትምህርት ደንቦች መምሪያ ስር ያሉትን የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ሙሉ ማብራሪያ የያዘ ማስታወቂያ እንዲሰጡ ያስገድዳል። የዚህ ማስታወቂያ ቅጂ ቢያንስ በአንድ የትምህርት ዘመን አንድ ጊዜ ለወላጆች መስጠት አለበት፣ እና ቅጂው ለወላጆች መሰጠት ያለበት፡- (1) በመጀመሪያ ሪፈራል ላይ ወይም ወላጅ ለግምገማ ሲጠይቅ፤ (2) በትምህርት ዘመኑ ውስጥ ከ 34 CFR 300.151 እስከ 300.153 (OAR 581-015-2030) መሰረት የመጀመሪያ የግዛት ልዩ ትምህርት ቅሬታ ቅበላ ላይ እና በ 300.507 (OAR 581-015-2345) መሰረት የመጀመሪያ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ቅበላ ላይ፤ (3) በልጅዎ ላይ የምደባ ለውጥ የሚያስከትል የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ ውሳኔ ሲደረግ፤ እና (4) በሚጠይቁበት ጊዜ።

በዚህ ሰነድ ውስጥ ያሉት ሁሉም መብቶች ከ IDEA ክፍል ለ ጋር የተያያዙ ናቸው። ክፍል ለ ከሶስት (3) እስከ ሃያ አንድ (21) አመት ያሉ ልጆችን ያጠቃልላል። እንዲሁም ODE በህጻናት አገልግሎት አቅርቦት/የቅድመ ልጅነት ልዩ ትምህርት (EI/ECSE) ፕሮግራሞች ውስጥ እድሜያቸው – አምስት (5) ለሆኑ ልጆች የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያዎችን ያትማል።

እንዲሁም ይህ የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያ በማንኛውም የኦሬገን ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ወላጆች ተግባራዊ ይሆናል። በኦሬገን ህግ መሰረት፣ የቻርተር ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዲስትሪክት ለልዩ ትምህርት ሃላፊነት አለበት።

## ቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ

### ማስታወቂያ

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት፣ የሚከተሉትን ከማድረጉ ተገቢ የሆነ የጊዜ መጠን በፊት፣ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል (በጽሁፍ የተረጋገጠ መረጃ ይሰጥዎታል)፡-

1. የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ፣ ወይም ትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦት ለመጀመር ወይም ለመቀየር ሃሳብ ማቅረብ፤ **ወይም**
2. የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ፣ ወይም ትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ለልጅዎ የFAPE አቅርቦትን ለመጀመር ወይም ለመለወጥ ፈቃደኛ ካልሆነ።

### የማስታወቂያ ይዘት

የጽሁፍ ማስታወቂያው የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

1. የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ያቀረበውን ወይም ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነውን እርምጃ መግለጽ፤
2. የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት እርምጃ ለመውሰድ ለምን ሃሳብ እንዳቀረበ ወይም ፈቃደኛ እንዳልሆነ ማብራራት፤
3. የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት እርምጃውን ለማቅረብ ወይም ላለመቀበል ሲወስን ጥቅም ላይ ያዋለውን እያንዳንዱን የግምገማ ሂደት፣ ግምገማ፣ መዝገብ፣ ወይም ሪፖርት መግለጽ፤
4. በ IDEA ክፍል ለ ውስጥ ባለው የሰራር ሂደት ጥበቃዎች አቅርቦቶች መሰረት ጥበቃዎች እንዳለዎት የሚገልጽ መግለጫ ማካተት፤
5. የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የሚያቀርበው ወይም የሚከለክለው እርምጃ ለግምገማ የመጀመሪያ ሪፈራል ካልሆነ የዚህን የሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያ ቅጂ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መንገር፤ IDEAን ለመረዳት እርዳታ ለማግኘት እንዲያነጋግሩ መረጃዎችን ማካተት፤
6. የልጅዎ የግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ያሰባቸውን ማናቸውንም ሌሎች አማራጮች እና እነዚያ አማራጮች ተቀባይነት ያላገኙበትን ምክንያቶች መግለጽ፤ **እና**
7. ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ፕሮፖዛል ወይም ፈቃደኛ ያለመሆን ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ ማቅረብ።

### መረዳት በሚቻልበት ቋንቋ ማስታወቂያ

ማስታወቂያው መሆን ያለበት፡-

**1.** ጠቅላላው ህዝብ መረዳት በሚችልበት ቋንቋ የተጻፈ፤ **እና**

2. ይህን ለማድረግ የማይቻል ካልሆን በስተቀር፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ በሚጠቀሙበት የግንኙነት ዘዴ የቀረበ።

የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም ሌላ የሚጠቀሙበት የግንኙነት ዘዴ የጽሁፍ ቋንቋ ካልሆነ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

1. ማስታወቂያው በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የግንኙነት ዘዴ ለእርስዎ በቃል መተርጎሙን፤
2. እርስዎ የማስታወቂያውን ይዘት መረዳትዎን፤ **<u>እና</u>**
3. ከላይ ያሉት 1 እና 2 መሟላታቸውን የሚያሳዩ የጽሁፍ ማስረጃዎች መኖራቸውን።

## <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ</u>

*የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣* የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታው ውስን ከሆነ ግለሰብ ጋር በሚጠቀሙበት ጊዜ፣ የሚከተለው ይሆናል ማለት ነው፡-

1. ቋንቋው በዚያ ሰው በመደበኛነት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ወይም፣ በልጁ ጉዳይ፣ ቋንቋው በልጁ ወላጆች በመደበኛነት ጥቅም ላይ ይውላል፤
2. ከልጁ ጋር በሁሉም ቀጥተኛ ግንኙነት (የልጁን ግምገማ ጨምሮ)፣ ቋንቋው በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት አካባቢ በልጁ በመደበኛነት ጥቅም ላይ ይውላል።

መስማት የተሳነው ወይም ለአይነ ስውር ለሆነ ሰው፣ ወይም የጽሁፍ ቋንቋ ለሌለው ሰው፣ የመገናኛ ዘዴው ግለሰቡ በመደበኛነት የሚጠቀመው (እንደ ምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል (የአይነ ስውራን ስርዐተ ጽህፈት)፣ ወይም የቃል ግንኙነት) ነው።

## <u>በሌክትሮኒክስ የሚላክ መልእክት</u>

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ለወላጆች ሰነዶችን በኢሜይል እንዲቀበሉ ምርጫ ካቀረበ፣ የሚከተሉትን በኢሜይል ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ፡-

1. ቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ
2. ይህንን የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያ፤ **<u>እና</u>**
3. ተገቢ ከሆነ የቅሬታ ሂደት ጋር የተያያዙ ማስታወቂያዎች።

***ማብራርያ***

*ስምምነት ማለት፡-*

1. *ፈቃድ ለሚሰጡበት እርምጃ ሁሉንም መረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ (እንደ ምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል (እንደ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል፣ ወይም የቃል ግንኙነት ያሉ) ሙሉ በሙሉ ተነግሮዎታል።*
2. *ያንን ተግባር በጽሁፍ ተረድተው ተስማምተዋል፣ እና ስምምነቱ ያንን ተግባር ይገልጻል እና የሚለቀቁትን መዝገቦች (ካሉ) እና ለማን እንደሆነ ይዘረዝራል፤* ***<u>እና</u>***
3. *ስምምነቱ በእርስዎ በኩል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና በማንኛውም ጊዜ ስምምነት ሊያነሱ እንደሚችሉ ተረድተዋል።*

***ስምምነትን መሻር*** - ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማግኘት ከጀመረ በኋላ የእርስዎን ስምምነት መሻር (መሰረዝ) ከፈለጉ፣ በጽሁፍ ማድረግ አለብዎት። የመውጣት ስምምነትዎ ስምምነትዎን ከሰጡ በኋላ የተከሰተውን ድርጊት እንጂ ከስምምነቱ መውጣትዎ በፊት ያለውን አይሰርዘውም (አይቀለብሰውም)። በተጨማሪ፣ ከስምምነትዎ ከወጡ በኋላ ልጅዎ ከልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የተቀበላቸውን ማናቸውንም ማጣቀሻዎች ለማጥፋት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የልጅዎን የትምህርት መዛግብት ማሻሻል (መቀየር) አይጠበቅበትም።

**ስምምነት**

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የስምምነት አቅርቦቶች ለአዋቂ ተማሪዎች እና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችም ላይ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ያስታውሱ።

***ለመጀመሪያ ግምገማ ስምምነት***

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ስለቀረበው ተግባር በቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሳይሰጥዎ እና ***በቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ*** *እና* ***ስምምነት*** ርእስ ስር እንደተገለጸው ፈቃድዎን ሳያገኝ ልጅዎን በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ መሆን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን የልጅዎን የመጀመሪያ ግምገማ ማካሄድ አይችልም።

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ልጅ መሆን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ለመጀመሪያ ግምገማ የእርስዎን በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ለማግኘት በቂ የሆነ ጥረት ማድረግ አለበት።

የመጀመሪያ ግምገማ ስምምነትዎ ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲጀምር ለትምህርት ዲስትሪክቱ ፈቃድዎን ሰጥተዋል ማለት አይደለም።

የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ ለአንድ አገልግሎት ወይም ተግባር ፈቃደኛ አለመሆንዎን ሌላ የክፍል ለ መስፈርት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ይህንን እንዲያደርግ ካላዘዘ በስተቀር፣ እርስዎን ወይም ልጅዎን ሌላ ማንኛውንም አገልግሎት፣ ጥቅማጥቅም፣ ወይም እንቅስቃሴ ለመከልከል እንደ መሰረት ሊጠቀምበት አይችልም።

ልጅዎ በህዝብ ትምህርት ቤት ከተመዘገበ ወይም ልጅዎን በህዝብ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ እየፈለጉ ከሆነ እና ለመጀመሪያ ግምገማ ስምምነት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ፈቃድ ለመስጠት ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ የIDEA ሽምግልና ወይም ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት፣ የመፍትሄ ስብሰባ፣ እና ገለልተኛ እገቢ የሆነ የችሎት ሂደቶችን በመጠቀም ለልጅዎ የመጀመሪያ ግምገማ ለማካሄድ ሊፈልግ ይችላል፣ ነገር ግን አይገደድም። የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ ልጅዎን በእነዚህ ሁኔታዎች ግምገማ ካልቀጠለ ልጅዎን የመፈለግ፣ የመለየት እና የመገምገም ግዴታዎቹን አይጥስም።

***በግዛቱ ጥበቃ ስር ለሆኑ የመጀመሪያ ግምገማ ልዩ ደንቦች***

አንድ ልጅ በግዛቱ ጥበቃ ስር ከሆነ እና ከወላጅ ጋር የማይኖር ከሆነ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጁ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ መሆኑን ለመወሰን ከወላጅ ፈቃድ አያስፈልገውም፡-

1. ይህን ለማድረግ ተገቢ የሆኑ ጥረቶች ቢደረጉም፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የልጁን ወላጅ ማግኘት አልቻለም፤
2. በግዛቱ ህግ ጋር የሚጣጣሙ የወላጆች መብቶች ተቋርጠዋል፤ ***<u>ወይም</u>***
3. አንድ ዳኛ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን እና ለመጀመሪያ ግምገማ ፈቃድ ለመስጠት ከወላጁ ውጪ

ለአንድ ግለሰብ መድቧል።

*በግዛቱ ጥበቃ ስር መሆን*፡ በIDEA ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው፣ ልጁ በሚኖርበት ግዛት በተወሰነው መሰረት፣ አንድ ልጅ ማለት፡-

1. የማደጎ ልጅ፤
2. ግዛቱ ህግ መሰረት የግዛቱ ጥበቃ ስር እንደሆነ የሚቆጠር፤ **<u>ወይም</u>**
3. በህዝብ የልጅ ደህንነት ድርጅት የማሳደግ ሃላፊነት ስር ያለ።

ማወቅ ያለብዎት አንድ የተለየ ነገር አለ። *በግዛቱ ጥበቃ ስር መሆን* በ IDEA ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው *የወላጅ* ትርጓሜን የሚያሟላ የማደጎ ወላጅ ያለውን የማደጎ ልጅ አያካትትም።

በኦሬገን ውስጥ፣ በግዛቱ ጥበቃ ስር የሆነው በጊዜአዊነት ወይም በቋሚነት በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ወይም በኦሬገን የወጣቶች ባለስልጣን በወጣቶች ፍርድ ቤት የማሳደግ ሃላፊነት ውስጥ ያለ ወይም የገባ ልጅ ነው።

**ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት**

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከመስጠቱ በፊት በመረጃ የተደገፈ ፈቃድዎን ማግኘት አለበት።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከመስጠቱ በፊት የእርስዎን በመረጃ የተደገፈ ፈቃድ ለማግኘት ተገቢ የሆነ ጥረት ማድረግ አለበት።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ፈቃድ እንዲሰጡ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ ወይም ይህንን ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም በኋላ ፈቃድዎን በጽሁፍ ከሻሩ (ከሰረዙ)፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ ለልጅዎ ልዩ ትምህርቱን እና ተዛማጅ አገልግሎቶቹን ያለ እርስዎ ስምምነት ሊሰጥ እንደሚችል የሚገልጽ (በልጅዎ IEP ቡድን የሚመከር) ስምምነት ወይም ውሳኔ ለማግኘት የአሰራር ሂደት ጥበቃዎችን (ማለትም ሽምግልና፣ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት፣ የመፍትሄ ስብሰባ፣ ወይም ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት) ላይጠቀም ይችላል።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ፈቃድዎን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ ወይም ይህንን ፈቃድ እንዲሰጡ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ ወይም በኋላ ፈቃድዎን በጽሁፍ ከሰረዙ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለልጅዎ ፈቃድ የጠየቀበትን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ካልሰጠ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት፡-

1. ለልጅዎ እነዚያን አገልግሎቶች ለልጅዎ ባለመሰጠቱ ምክንያት ነጻ ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንዲያገኝ ለማድረግ የተቀመጠውን መስፈርት የሚጥስ አይደለም፤ **<u>እና</u>**
2. ፈቃድዎ ለተጠየቀባቸው ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ማድረግ ወይም ለልጅዎ IEPን ለማዘጋጀት አይጠበቅበትም።

መጀመሪያ ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ከተሰጠ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድዎን በጽሁፍ ከሻሩ (ከሰረዙ)፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እንደዚህን አገልግሎቶችን መስጠት ላይቀጥል ይችላል፣ ነገር ግን ***ቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ እነዚያን አገልግሎቶች ከማቋረጡ በፊት፣ ቀዳሚ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል፣

**ለዳግም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት**

የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የሚከተሉትን ካልገለጸ በስተቀር፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ልጅዎን እንደገና ከመገምገሙ በፊት በመረጃ የተደገፈ ስምምነትዎን ማግኘት አለበት፡-

1. ለዳግም ግምገማው የእርስዎን ስምምነት ለማግኘት ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ወስዷል፤ **<u>እና</u>**
2. እርስዎ ምላሽ አልሰጡም።

የኦሬገን ህግ ለማንኛውም የግለሰብ የማገናዘብ መመዘኛ ወይም የስብዕና መመዘኛ በመረጃ የተደገፈ የጽሁፍ ፈቃድ ያስፈልገዋል፤ ለእነዚህ ለሁለቱም ግምገማዎች ፈቃድ ሲጠይቁ የስምምነት ልዩነት ተግባራዊ አይሆንም።

ለልጅዎ ዳግም ግምገማ ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለልጅዎ ዳግም ግምገማ ፈቃደኛ አለመሆንዎን ለመለወጥ ሽምግልና፣ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት፣ የመፍትሄ ስብሰባ እና ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት አሰራሮችን በመጠቀም ዳግም ግምገማውን ሊከታተል ይችላል፤ ነገር ግን አይገደድም። እንደ መጀመሪያ ግምገማዎች፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት በዚህ መልኩ ዳግም ግምገማውን ለመከታተል ፈቃደኛ ካልሆነ በ IDEA ክፍል ለ ስር ያሉትን ግዴታዎች አይጥስም።

**ፈቃድ ለማግኘት የዋሉ ተገቢ ጥረቶች የሚያሳዩ ሰነዶች**

ትምህርት ቤትዎ ለመጀመሪያ ግምገማዎች ፈቃድዎን ለማግኘት፣ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመስጠት፣ ለዳግም ግምገማ፣ እና ለመጀመሪያ ግምገማዎች በግዛቱ ጥበቃ ስር ለሆኑ ወላጆችን ለማግኘት የሚያደርገውን ሙከራ መመዝገብ አለበት። ሰነዱ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በእነዚህ ዙሪያ ያደረጋቸውን ሙከራዎች መዝገብ ማካተት አለበት፣ ለምሳሌ፦

1. የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች እና የእነዚያን ጥሪዎች ውጤቶች ዝርዝር መዛግብት፤
2. ለወላጆች የተላኩ የደብዳቤ ቅጂዎች እና ማንኛውም የደረስዎት ምላሾች፤ <u>እና</u>
3. ወደ ወላጅ ቤት ወይም የስራ ቦታ የተደረጉ ጉብኝቶች ዝርዝር መዛግብት እና የእነዚያ ጉብኝቶች ውጤቶች።

**ሌሎች የስምምነት መስፈርቶች**

የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ የሚከተሉትን ከማድረጉ በፊት የእርስዎ ፈቃድ አይጠየቅም፦

1. እንደ ልጅዎ ግምገማ ወይም የዳግም ግምገማ አካል ያለውን ውሂብ መገምገም፤
2. ከዚያ ፈተና ወይም ግምገማ በፊት፣ ከሁሉም ልጆች ወላጆች ፈቃድ ካልተጠየቀ በስተቀር፣ ለሁሉም ልጆች የሚሰጥ ምዘና ወይም ሌላ ግምገማ መስጠት፤

ልጅዎን በራስዎ ወጪ በግል ትምህርት ቤት ካስመዘገቡ ወይም ልጅዎን ቤት ውስጥ እያስተማሩ ከሆነ፣ እና ለልጅዎ የመጀመሪያ ግምገማ ወይም የልጅዎ ዳግም ግምገማ ፈቃድዎን ካልሰጡ፣ ወይም ስምምነትዎን ለማቅረብ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የስምምነት መሻር ሂደቶች (ማለትም ፣ ሽምግልና፣ ገለልተኛ የፍትህ ሂደት ችሎት) ላይጠቀም ይችላል እና ልጅዎን ፍትሃዊ አገልግሎቶች ለማግኘት በብቁነት ግምት ውስጥ ለማስገባት አይገደድም (አገልግሎቶቹ ለአንዳንድ በወላጅ የተመደቡት የአካል ጉዳተኛ የግል ትምህርት ቤት ልጆች ቀርቧል)።

**የህዝብ ጥቅማጥቅሞችን እና ኢንሹራንስን ለመጠቀም (እንደ Medicaid ያሉ) ስምምነት**

ከነዚህ ለማናቸውም አገልግሎቶች እና ተግባራት ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ልጅዎ የሚያገኘውን ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንደማያስቀር ለማረጋገጥ የትምህርት ዲስትሪክቱ ሂደቶችን ማዘጋጀት እና መተግበር አለበት። እንዲሁም፣ ሌላ የክፍል ለ መስፈርት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክ ይህንን እንዲያደርግ ካላስገደደ በስተቀር፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ከእነዚህ አገልግሎቶች ወይም ተግባራት ውስጥ አንዱን ለመጠቀም ፈቃደኛ አለመሆንዎን ሌላ ማንኛውንም አገልግሎት፣ ጥቅማጥቅም፣ ወይም ተግባር ላለመስጠት እንደ መሰረት ላይጠቀምበት ይችላል።

በማንኛውም ጊዜ ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በጽሁፍ በማሳወቅ ስምምነትን መሻር ይችላሉ። ስምምነትዎን ከሰረዙ፣ ልጅዎ FAPE ለመስጠት የሚያያስፈልገውን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ያገኛል።

## <u>ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች (IEE)</u>

**አጠቃላይ**

ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣ በትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ በተገኘው የልጅዎ ግምገማ ካልተስማሙ ለልጅዎን ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች (IEE) የማግኘት መብት አለዎት።

IEE ከጠየቁ፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት IEE የት ማግኘት እንደሚችሉ እና ለገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማዎች ተግባራዊ ስለሚሆን የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት መስፈርት መረጃ መስጠት አለበት።

**ማብራርያዎች**

*ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ* ማለት ለልጅዎ ትምህርት ሃላፊነት በሚወስድ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ባልተቀጠረ ብቃት ባለው ፈታኝ የሚካሄድ ግምገማ ነው።

*የህዝብ ወጪ* ማለት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፣ ለግምገማው ሙሉ ወጪ ይከፍላል ወይም በሌላ መንገድ ግምገማው ያለ ምንም ወጪ ለእርስዎ መሰጠቱን ያረጋግጣል፣ የህግ ክፍል ለ መስፈርቶችን ለሟሟላት እያንዳንዱ ግዛት፣ የትኛውንም በግዛቱ ውስጥ የሚገኙ፣ ከIDEA ክፍል ለ አቅርቦቶች ጋር የሚጣጣሙ የግዛት፣ የአካባቢ፣ የፌደራል እና የግል ድጋፍ ምንጮች እንዲጠቀም ያስችለዋል።

**በሕዝብ ወጪ የመገምገም መብት**

በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት፣ በትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት በተገኘው የልጅዎ ግምገማ ካልተስማሙ በህዝብ ወጪ ለልጅዎ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አለዎት፦

1. በህዝብ ወጪ ለልጅዎ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቁ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት፣ ያለ አላስፈላጊ መዘግየት፣ <u>ወይ</u>፦ (ሀ) የልጅዎ ግምገማው ተገቢ መሆኑን ለማሳየት ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ማቅረብ፤ <u>ወይም</u> (ለ)የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ያገኙት የልጅዎ ግምገማ የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በችሎት ካላሳየ በስተቀር፣ በህዝብ ወጪ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ማቅረብ አለበት።

2. የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ችሎት ከጠየቀ እና የመጨረሻው ውሳኔ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ለልጅዎ የሰጠው ግምገማ ተገቢ ከሆነ፣ አሁንም ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አለዎት ነገር ግን በህዝብ ወጪ አይደለም።

3. ለልጅዎ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቁ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የተገኘውን ግምገማ ለምን እንደተቃወሙ ሊጠይቅ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ማብራሪያ ላያስፈልገው ይችላል እና ያለምክንያት በህዝብ ወጪ ለልጅዎ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ለማቅረብ ወይም የተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት በማቅረብ የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት የልጅዎን ግምገማ ለማስከበር ላይዘገይ ይችላል።

የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እርስዎ የማይስማሙበት የልጅዎን ግምገማ በሚያካሂድበት እያንዳንዱ ጊዜ ለልጅዎ በህዝብ ወጪ ለሚደረግ አንድ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ብቻ መብት ተሰጥቶታል።

### በወላጆች የተጀመሩ ግምገማዎች

በህዝብ ወጪ የልጅዎን ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ካገኙ ወይም በግል ወጪ ያገኙትን የልጅዎን ግምገማ ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ካጋሩ፦

1. ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በተመለከተ በሚደረጉ በማናቸውም ውሳኔዎች፣ ለገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት መስፈርት ካሟላ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የልጅዎን የግምገማ ውጤት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤ <u>**እና**</u>

2. እርስዎ ወይም የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ልጅዎን በሚመለከት እገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ግምገማውን እንደ ማስረጃ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

### በችሎት ሂደት ባለስልጣናት የግምገማ ጥያቄዎች

የችሎት ሂደት ባለስልጣን እንደ ተገቢ የችሎት ሂደት አካል የልጅዎን ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ ከጠየቀ፣ የግምገማው ወጪ በህዝብ ወጪ መሆን አለበት።

### የትምህርት ቤት ዲስትሪክት መስፈርቶች

ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ በህዝብ ወጪ ከሆነ፣ ግምገማው የሚገኝበት መስፈርት፣ የግምገማው ቦታ እና የፈታኙን መመዘኛዎች ጨምሮ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ግምገማ ሲጀምር ከሚጠቀመው መስፈርት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት (እነዚያ መስፈርቶች ከገለልተኛ ትምህርታዊ ግምገማ መብትዎ ጋር በመጠን የሚጣጣሙ ናቸው)።

ከላይ ከተገለጸው መስፈርት በስተቀር፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በህዝብ ወጪ ገለልተኛ ትምህርታዊ ግምማ ከማግኘት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ወይም የጊዜ ገደቦችን ሊያወጣ አይችልም።

# የመረጃ ምስጢራዊነት

## የምስጢራዊነት ማብራርያዎች

**የመረጃ ሚስጥራዊነት** በሚለው ርዕስ ስር ጥቅም ላይ እንደዋለ፡-

- *ማጥፋት* ማለት አካላዊ ጥፋት ወይም የግል መለያዎችን ከመረጃ ማስወገድ ነው፤ ስለዚህም መረጃው በግል ለመለየት የማይቻል ይሆናል።
- *የትምህርት መዛግብት* ማለት በ34 CFR ክፍል 99 (የ1974 የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግን የሚተገብሩ ደንቦች፣ 20 U.S.C. § 1232g (FERPA)) እና OAR 581-015-2300 "በትምህርት መዛግብት" ትርጓሜ ስር የተሸፈኑ የመዛግብት አይነት ማለት ነው።
- *ተሳታፊ ድርጅት* ማለት ማንኛውም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት፣ ድርጅት ወይም ተቋም በግል መለየት የሚቻል መረጃን የሚሰበስብ፣ የሚይዝ፣ ወይም የሚጠቀም፣ ወይም በ IDEA ክፍል ለ መሰረት፣ መረጃ የተገኘበት ማለት ነው።

## በግል መለየት የሚቻል

*በግል መለየት የሚቻል* ማለት የሚከተሉትን የሚያካትት መረጃ ማለት ነው፡-

(a) የልጅዎ ስም፣ እንደ ወላጅ የእርስዎ ስም፣ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ስም፤

(b) የልጅዎ አድራሻ፤

(c) እንደ የልጅዎ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር፣ የተማሪ ቁጥር ወይም የባዮሜትሪክ ቁጥር ያለ የግል መለያ፤

(d) ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ መለያዎች፣ ለምሳሌ የልጁ የትውልድ ቀን፣ የትውልድ ቦታ እና ያገባች ሴት የመጀመሪያ የአባት ስም፤
የመጀመሪያ የአባትዋ ስም፤

(e) በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ተገቢ የሆነን ሰው፣ ተዛማጅ ሁኔታዎችን በተመለከተ የግል እውቀት የሌለው፣ አንድ ልጅን በተመጣጣኝ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችል ብቻውን ያለ ወይም ሌላ ጥምር መረጃ፤ ወይም

(f) የትምህርት መዝገቡ በዝርዝር ለመንገር የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የተማሪውን ማንነት እንደሚያውቅ በምክንያታዊነት በሚያምነው ሰው የተጠየቀ ሌላ መረጃ።

## ማስታወቂያ ለወላጆች

SEA የሚከተሉትን ጨምሮ፣ በግል መለየት የሚቻል የመረጃ ሚስጥራዊነትን በተመለከተ ለወላጆች ሙሉ ለሙሉ ለማሳወቅ በቂ የሆነ ማሳሰቢያ መስጠት አለበት፡-

1. ግዛቱ ውስጥ ባሉ የተለያዩ የህዝብ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ማስታወቂያው ምን ያህል መጠን እንደተሰጠ መግለጫ፤
2. በግል መለየት የሚችል መረጃ የሚተዳደርባቸው ልጆች መግለጫ፣ የሚፈለጉት የመረጃ አይነቶች፣ ግዛቱ መረጃውን በመሰብሰብ ጥቅም ላይ ለማዋል ያሰባቸውን ዘዴዎች (መረጃ የሚሰበሰብባቸውን ምንጮች ጨምሮ)፣ እና መረጃውን ለመጠቀም ስለሚጠቀሙባቸው መንገዶች መግለጫ፤
3. በግል የሚለይ መረጃ ማከማቻን፣ ለሶስተኛ ወገኖች ይፋ ማድረግን፣ ማቆየትን እና መጥፋትን በተመተለከተ ተሳታፊ ድርጅቶች መከተል ያለባቸው ፖሊሲዎች እና ሂደቶች ማጠቃለያ፤ **<u>እና</u>**
4. በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) እና በ 34 CFR ክፍል 99 ውስጥ ያሉትን የአፈጻጸም ደንቦቹን ጨምሮ፣ ይህንን መረጃ በተመለከተ የወላጆች እና የልጆች መብቶች መግለጫ።

ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ለመለየት፣ ለማግኘት ወይም ለመገምገም (እንዲሁም "የልጅ ማግኘት" በመባል የሚታወቅ) ከማንኛውም ትልቅ ተግባር በፊት፣ ማስታወቂያው፣ የእነዚህን ተግባራት ሁኔታ ለወላጆች ለማሳወቅ በቂ ስርጭት ባለው፣ በጋዜጣ ወይም በሌላ ሚዲያ ወይም፣ በሁለቱም መታተም ወይም መታወጅ አለበት።

**የመዳረሻ መብቶች**

ተሳታፊው ድርጅት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት በትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት የሚሰበሰቡ፣ የሚጠበቁ፣ ወይም ጥቅም ላይ የሚውሉ ከልጅዎ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም የትምህርት መዝገቦችን እንዲመረምሩ እና እንዲገመግሙ መፍቀድ አለበት። ተሳታፊው ድርጅት በልጀዎ ላይ ያሉ ማናቸውንም የትምህርት መዛግብት ያለ ምንም አላስፈላጊ መዘግየት እና የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፣ ወይም ማንኛውንም ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት (የመፍትሄ ስብሰባ ወይም ቅጣትን በሚመለከት ችሎትን ጨምሮ) በሚመለከት ከማንኛውም ስብሰባ በፊት ለመመርመር እና ለመገምገም እና በምንም ሁኔታ ጥያቄ ካቀረቡ ከ45 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ያቀረቡትን ጥያቄ ማክበር አለበት።

የትምህርት መዝገቦችን የመመርመር እና የመገምገም መብትዎ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

1. ስለ መዛግብቱ ማብራሪያ እና ትርጓሜዎች ምክንያታዊ ለሆኑ ጥያቄዎች ከተሳታፊ ድርጅት ዲስትሪክ ምላሽ የማግኘት መብትዎን፤
2. እነዚያ ቅጂዎች ካልተቀበሉ በስተቀር መዛግብቱን በብቃት መመርመር እና መገምገም ካልቻሉ ተሳታፊው ድርጅት የመዛግብቱን ቅጂዎች እንዲሰጥዎ የመጠየቅ መብትዎን፤ <u>**እና**</u>
3. መዛግብቱን እንዲመረምር እና እንዲገመግም ተወካይዎን የማግኘት መብትዎን።

---

[የ] U.S. የትምህርት መምሪያ *"ተሳታፊ ድርጅት" የሚለውን ቃል በግል መለየት የሚቻል መረጃን የሚሰበስብ፣ የሚይዝ፣ ወይም የሚጠቀም ወይም በIDEA ክፍል ለ መሰረት መረጃ የሚገኝበት ማንኛውንም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት፣ ድርጅት፣ ወይም ተቋምለማለት ይጠቀምበታል።* ይህ ሰነድ የሚያተኩረው ወላጅ በአካባቢው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በሚኖረው ተሳትፎ ላይ ስለሆነ፣ "ተሳታፊ ድርጅት"፣ ከሚለው ከሰፊው ቃል ይልቅ "የትምህርት ቤት ዲስትሪክት" ጥቅም ላይ ይውላል፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ክፍል የተብራሩት የመዛግብት ደንቦች በሁሉም ተሳታፊ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

እንደ አሳዳጊነት፣ መለያየት፣ እና ፍቺ ያሉ ጉዳዮችን በሚወስነው የሚተገበር የግዛት ህግ መሰረት ስልጣን እንደሌለዎት መረጃ ካልደረስዎት በስተቀር ተሳታፊው ድርጅት ከልጅዎ ጋር የተዛመዱ መዝገቦችን የመመርመር እና የመገምገም ስልጣን እንዳለዎት ሊገምት ይችላል።

## የመዳረሻ መዝገብ

እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት (ከወላጆች እና የተሳታፊው ድርጅት ፈቃድ ያላቸው ሰራተኞች ከሚገኙ ውጪ) የተሰበሰቡ፣ የተያዙ፣ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት መዛግብትን የሚያገኙ አካላትን፣ የሶስተኛ ወገኑን ስም፣ መዳረሻ የተሰጠበት ቀን፣ እና ሶስተኛ ወገኑ መዝገቦቹን ለመጠቀም የተፈቀደለትን አላማ ጨምሮ መዝግቦ መያዝ አለበት።

## ከአንድ በላይ ልጆች የሚያመለክቱ መዛግብት

ማንኛውም የትምህርት መዝገብ ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆችን መረጃ የሚያካትት ከሆነ፣ የእነዚያ ልጆች ወላጆች ከልጃቸው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ብቻ የመመርመር እና የመገምገም ወይም ስለዚያ የተለየ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው።

## የመረጃ ዓይነቶች እና ቦታዎች ዝርዝር

በተጠየቀ ጊዜ፣ ተሳታፊው ድርጅት በድርጅቱ የተሰበሰቡ፣ የተያዙ፣ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት መዛግብት አይነቶች እና ቦታዎች ዝርዝር ሊሰጥዎ ይገባል።

## ክፍያዎች

ክፍያው እነዚያን መዛግብት የመመርመር እና የመገምገም መብትዎን ውጤታማ በሆነ መንገድ ከመጠቀም የሚከላከል ካልሆነ፣ እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ለእርስዎ ለተሰሩት የመዛግብት ቅጂዎች ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል።

አንድ ተሳታፊ ድርጅት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት መረጃን ለመፈለግ ወይም ለማግኘት ክፍያ ላያስከፍል ይችላል።

## በወላጆች ጥያቄ መዛግብትን ማሻሻል

በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ልጅዎን በሚመለከት በትምህርት መዛግብት ላይ ያለው የተሰበሰበው፣ የተያዘው፣ ወይም ጥቅም ላይ የዋለው መረጃ የተሳሳተ፣ አሳሳች፣ ወይም የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶችን የሚጥስ መሆኑን ካመኑ፣ መረጃውን ለመለወጥ መረጃውን የሚይዘውን ተሳታፊ ድርጅትን መጠየቅ ይችላሉ።

ተሳታፊው ድርጅት ጥያቄው በደረሰው በተገቢው ጊዜ ውስጥ በጥያቄዎ መሰረት መረጃውን ለመቀየር ወይም ላለመቀየር መወሰን አለበት።

ተሳታፊው ድርጅት በተጠየቀው መሰረት መዝገቡን ላለማሻሻል ከወሰነ፣ ስለ ውሳኔው ማሳወቅ እና ***የችሎት ሂደት የመስጠት እድል*** በሚለው ስር እንደተገለጸው ችሎት የማግኘት መብት እንዳለዎት ምክር መስጠት አለበት።

**የችሎት ሂደት የማቅረብ እድል**

የተጠየቀው፣ ተሳታፊው ድርጅት ልጅዎን በሚመለከቱ ምክንያቶች በትምህርት መዛግብት ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች፣ ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ በመሆኑ ለመቃወም የችሎት ሂደት እድል ሊሰጥዎ ይገባል።

**የችሎት አሰራር ሂደቶች**

በትምህርት መዝገቦች ውስጥ ያለውን መረጃ ለመቃወም የችሎት ሂደት መከናወን ያለበት በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግ (FERPA) ስር ባሉ ችሎቶች አሰራር መሰረት ነው።

**የችሎት ሂደት ውጤቶች**

በችሎቱ ምክንያት ተሳታፊው ኤጀንሲ መረጃው ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም በሌላ መንገድ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚጥስ መሆኑን ከወሰነ መረጃውን በዚሁ መሰረት ቀይሮ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

በችሎቱ ምክንያት፣ ተሳታፊው ድርጅት መረጃው ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም በሌላ መንገድ የልጅዎን ግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶችን የሚጥስ አለመሆኑን ከወሰነ፣ በልጅዎ ላይ በመረጃው ላይ አስተያየት የሚሰጥ መግለጫ ወይም በተሳታፊ ድርጅቱ ውሳኔ የማይስማሙበትን ምክንያት እንደሚያቀርብ በመዝገቡ ውስጥ የማስቀመጥ መብት እንዳለዎት ማሳወቅ አለበት።

በልጅዎ መዝገብ ውስጥ የተቀመጠው እንደዚህ አይነቱ ማብራሪያ የሚለተለውን መከተል ይኖርበታል፡-

1. መዝገቡ ወይም ክርክር የተደረገበት ክፍል በተሳታፊው ድርጅት እስከተያዘ ድረስ እንደ የልጅዎ መዛግብት አካል በተሳታፊው ድርጅት ይያዛል፤ **<u>እንዲሁም</u>**
2. ተሳታፊው ድርጅት የልጅዎን መዛግብት ወይም የተከራካሪውን መረጃ ለማንኛውም አካል ይፋ ካደረገ፣ ማብራሪያውም ለዚያ አካል መገለጽ አለበት።

**በግል ሊታወቅ የሚቻል መረጃን ይፋ የማድረግ ስምምነት**

መረጃው በትምህርት መዛግብት ውስጥ እስካልተያዘ ድረስ: እና በይፋ የመታወቁ ጉዳይ በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) መሰረት ያለ ወላጅ ስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር፣ በግል የሚለይ መረጃ ከተሳታፊ ድርጅቶች ባለስልጣናት ውጪ ለሌላ አካላት ይፋ ከመሆኑ በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለበት። ከዚህ በታች ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር፣ የ IDEA ክፍል ለ መስፈርትን ለማሟላት አላማዎች በግል የሚለይ መረጃ ለተሳታፊ ድርጅቶች ባለስልጣናት ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ፈቃድ አያስፈልግም።

ለሽግግር አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ለሚከፍሉ የተሳታፊ ድርጅቶች ባለስልጣናት በግል የሚለይ መረጃ ከመለቀቁ በፊት የእርስዎ ፈቃድ፣ ወይም በግዛቱ ህግ መሰረት ለአካለ መጠን ከደረሰ ብቁ የሆነ ልጅ ፈቃድ፣ ማግኘት አለበት። ልጅዎ እርስዎ በሚኖሩበት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ከሌለ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ካለ ወይም ሊሄድ ከሆነ፣ ስለ ልጅዎ ማንኛውም በግል ሊለይ የሚችል መረጃ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ውስጥ ባሉ ባለስልጣናት ይኸውም የግል ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት እና እርስዎ የሚኖሩበት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ባለስልጣናት መካከል ከመለቀቁ በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለበት።

ልጅዎ እርስዎ በሚኖሩበት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ከሌለ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ካለ ወይም ሊሄድ ከሆነ፣ ስለ ልጅዎ ማንኛውም በግል ሊለይ የሚችል መረጃ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ውስጥ ባሉ ባለስልጣናት ይኸውም የግል ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት እና እርስዎ የሚኖሩበት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ባለስልጣናት መካከል ከመለቀቁ በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለበት።

## ጥበቃዎች

እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት በግል የሚለይ መረጃን በመሰብሰብ፣ በማከማቸት፣ ይፋ በሚያደረግበት እና በመጥፋት ደረጃዎች ላይ ሚስጥራዊነትን መጠበቅ አለበት።

በእያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት ውስጥ ያለ ባለስልጣን ማንኛውንም በግል የሚለይ መረጃን ሚስጥራዊነት ለማረጋገጥ ሃላፊነት መውሰድ አለበት።

በግል የሚለይ መረጃን የሚሰበስቡ ወይም የሚጠቀሙ ሁሉም ሰዎች በ IDEA ክፍል ለ እና በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) መሰረት ሚስጥራዊነትን በሚመለከት የግዛት ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን በተመለከተ ስልጠና ወይም መመሪያ ማግኘት አለባቸው።

እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት፡ ለህዝብ ምርመራ፣ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ በግል ሊለይ የሚችል መረጃ ሊያገኙ የሚችሉትን ሰራተኞች ስም እና የስራ ደረጃዎች ወቅታዊ ዝርዝር መያዝ አለበት።

## መረጃን ማጥፋት

በIDEA ክፍል ለ መሰረት የተሰበሰበ፣ የተያዘ፣ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ በግል የሚለይ መረጃ ከዚህ በኋላ ለልጅዎ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የማያስፈልግ ከሆነ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ለእርስዎ ማሳወቅ አለበት።

በእርስዎ ጥያቄ መሰረት መረጃው መጥፋት አለበት። ይሁን እንጂ፡ የልጅዎ ስም፣ አድራሻ ፣ እና ስልክ ቁጥር፣ የፈተና ውጤታቸው፣ የተሳትፎ መዝገብ፣ የተማሩባቸው ክፍሎች፣ ያጠናቀቁት የክፍል ደረጃ፣ እና የተጠናቀቀው አመት የሚገኝበት ቋሚ መዝገብ ያለ ጊዜ ገደብ ሊቆይ ይችላል። እርስዎ
የልጅዎ መረጃ በማይፈለግበት ጊዜ የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት እንዲያጠፋው
የመጠየቅ መብት አለዎት።

# አለመግባባቶችን መፍታት

## ሽምግልና

### አጠቃላይ

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ከመቅረቡ በፊት የሚነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ አለመግባባቶችን ለመፍታት እንዲችሉ፣ ሽምግልና በ ODE በኩል ይገኛል። ስለዚህ: ***ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ለመጠየቅ፡ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ቢያቀርቡ ወይም ባያቀርቡም፡ ወይም የትምህርት ቅሬታ ካስገቡ፡ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት አለመግባባቶችን ለመፍታት ሽምግልና ይኖራል።

### መስፈርቶች

የሂደቱ አሰራር የሽምግልና ሂደትን የሚከተሉት እንደሚያሟላ ማረጋገጥ አለበት፡-

1. በእርስዎ በኩል እና በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በኩል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፤
2. ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት የማግኘት መብትዎን ለመከልከል ወይም ለማዘግየት፣ ወይም በ IDEA ክፍል ለ ስር የተሰጡ ሌሎች መብቶችን ለመከልከል ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፤ **እንዲሁም**

3. በውጤታማ የሽምግልና ቴክኒኮች በሰለጠነ ብቁ እና ገለልተኛ ሽማግሌ የሚመራ ነው።

ግዛቱ የልዩ ትምህርትን እና የተዛማጅ አገልግሎቶችን አቅርቦት የሚዛመዱ ህጎችን እና ደንቦችን የሚያውቁ ሰዎችን እና ብቁ የሆኑ የሽማግሌ ሰዎችን ዝርዝር መያዝ አለበት። ግዛቱ ሽማግሌዎችን በዘፈቀደ፣ በተዘዋዋሪ ወይም በሌላ ገለልተኛ መሰረት ላይ መምረጥ አለበት።

ግዛቱ የስብሰባ ወጪዎችን ጨምሮ፣ ለሽምግልና ወጪዎች ሃላፊነት አለበት።

በሽምግልና ሂደት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ስብሰባ በጊዜ መርሃ ግብር መቀጠር እና ለእርስዎ እና ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ምቹ በሆነ ቦታ መካሄድ አለበት።

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት አለመግባባቶችን በሽምግልና ሂደት ከፈቱ፣ ሁለቱም ወገኖች መፍትሄውን የሚገልጽ ህጋዊ አስገዳጅ ስምምነት ውስጥ መግባት አለባቸው፡ እንዲሁም:-

1. በሽምግልና ሂደት ውስጥ የተከሰቱት ሁሉም ውይይቶች ሚስጥራዊ ሆነው እንደሚቆዩ እና በኋላ በሚመጣ ማንኛውም ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ወይም የፍትህ ብሄር ችሎት (የፍርድ ቤት ጉዳይ) እንደ ማስረጃ ሊጠቀሙ እንደማይችሉ ይገልጻል፤ **<u>እንዲሁም</u>**
2. በሁለታችሁም በእርስዎ እና የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት የማስገደድ ስልጣን ባለው የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተወካይ ተፈርሟል።

ተጽፎ፣ የተፈረመ የሽምግልና ስምምነት በማንኛውም የግዛት ፍርድ ቤት (ይህን አይነት ጉዳይ ችሎት ለመስማት በግዛቱ ህግ መሰረት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ተፈጻሚ ነው።

በሽምግልና ሂደት ውስጥ የተደረጉት ውይይቶች ሚስጥራዊ መሆን አለባቸው። ወደ ፊት በማንኛውም ተገብቢ የሆነ የችሎት ሂደት ውስጥ ወይም በማንኛውም የፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤት በIDEA ክፍል ለ መሰረት እርዳታ በሚያደርግ የፍትሃብሄር ችሎት ሂደት ውስጥ እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ ሊዉሉ አይችሉም።

**የሽማግሌ ገለልተኛነት**

ሽማግሌው:-

1. በልጅዎ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ውስጥ የተሳተፈ የSEA ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኛ ላይሆን ይችላል፤ **<u>እንዲሁም</u>**
2. ከሽማግሌው ፍርድ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም ሙያዊ ጥቅም ሊኖረው አይገባም።

በሌላ መልኩ ለሽምግልና ብቁ የሆነ ሰው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ወይም የግዛት ድርጅት ሰራተኛ ብቻ አይደለም ምክንያቱም እሱን ወይም እሷን እንደ ሽማግሌ ለማገልገል በድርጅቱ ስለሚከፈላቸው ነው።

# የግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶች

## በሂደት ላይ ያሉ ተገቢ ቅሬታዎች እና ችሎቶች እንዲሁም የግዛት ቅሬታዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች

የ IDEA ክፍል ለ ደንቦች ለግዛት ቅሬታዎች እና ተገቢ ለሆኑ የቅሬታዎች ሂደት እና ችሎቶች የተለዩ የአሰራር ሂደቶችን ይገልጻል። ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በትምህርት ቤት ዲስትሪክት፣ በ SEA ወይም በሌላ ማንኛውም የህዝብ ድርጅት የክፍል ለ መስፈርት መጣሱን በግልጽ በማሳወቅ የግዛት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። የአካል ጉዳተኛ ልጅን መለያ፣ ግምገማ፣ ወይም የአካል ጉዳተኛ ህጻን ትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ለልጁ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት አቅርቦት (FAPE) ጋር በተያያዘ ማንኛውም ጉዳይ ለማቅረብ ወይም ለመከልከል እርስዎ ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ ብቻ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

የ SEA ሰራተኞች በአጠቃላይ የግዛት ቅሬታን በ60 የቀን መቁጠሪያ ጊዜ ውስጥ በሚፈቱበት ጊዜ፣ የጊዜ ሰሌዳው በትክክል ካልተራዘመ በስተቀር፣ ገለልተኛ የችሎት ሂደት መኮንን (የአስተዳደር ህግ ዳኛ ወይም ALJ ተብሎ ይጠራል) ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደትን መስማት አለበት (በመፍትሄ ስብሰባ ወይም በሽምግልና ካልተፈታ) እና በዚህ ሰነድ፣ በመፍትሄ ሂደት ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ የችሎት መኮንኑ በእርስዎ ጥያቄ ወይም በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክጥ ጥያቄ የተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ካልፈቀደ በስተቀር፣ የመፍትሄው ጊዜ ካለቀ በኋላ በ 45 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል።

የግዛት ቅሬታ እና ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት፣ የመፍትሄ እና የችሎት ሂደቶች ከዚህ በታች በተሟላ መልኩ ተገልጸዋል። SEA ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት እንዲያቀርቡ ለማገዝ እና እርስዎ ወይም ሌሎች ወገኖች ***የሞዴል ቅጾች*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው የግዛት ቅሬታ እንዲያቀርቡ ለማገዝ ሞዴል ቅጾችን ማዘጋጀት አለበት።

## የግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶችን መቀበል

### አጠቃላይ

እያንዳንዱ SEA ለሚከተሉት ሂደቶች የተጻፈ የአሰራር ሂደት ሊኖረው ይገባል:-

1. ከሌላ ግዛት ከመጣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ያቀረበውን ቅሬታ ጨምሮ፣ ማንኛውንም የልዩ ትምህርት ቅሬታን መፍታት፤ እና
2. ለ SEA ቅሬታ ማቅረብ።
3. የግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶችን ለወላጆች እና ሌሎች ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች፣ በወላጅ ማሰልጠኛ እና የመረጃ ማዕከላት፣ በጥበቃ እና የጥብቅና ድርጅቶች፣ በገለልተኛ የመኖሪያ ማዕከላት፣ እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ አካላትን ጨምሮ በሰፊው ማሰራጨት።

### ተገቢውን አገልግሎት ባለመስጠት ምክንያት መፍትሄዎችን ማቅረብ

SEA ተገቢ የሆነ አገልግሎቶችን ባለመስጠቱ ለግዛት ቅሬታዎች መፍትሄ ለመስጠት፣ SEA የሚከተሉትን መፍታት አለበት:-

1. የህጻኑን ፍላጎቶች (እንደ ማካካሻ አገልግሎቶች ወይም የገንዘብ ማወራረጃ ያሉ) ተገቢ የሆኑ የማስተካከያ እርምጃዎችን ጨምሮ ተገቢ አገልግሎቶችን አለመስጠት፤ **<u>እና</u>**
2. ለሁሉም አካል ጉዳተኛ ልጆች ተገቢ የሆነ የወደፊት አገልግሎት አቅርቦት ።

## ዝቅተኛ የግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶች

### የጊዜ ገደብ፤ ዝቅተኛ ሂደቶች

እያንዳንዱ SEA በግዛቱ የቅሬታ አሰራር ሂደቶች ውስጥ ቅሬታ ከቀረበ በኋላ 60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ገደብ ማካተት አለበት:-

1. SEA ምርመራ አስፈላጊ መሆኑን ከተወሰነ፣ ገለልተኛ የሆነ ምርመራ ማካሄድ፤
2. ቅሬታ አቅራቢው በቅሬታው ውስጥ ስላሉት ክሶች፣ በቃልም ወይም በጽሁፍ፣ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ እድል መስጠት፤
3. ለቅሬታው ምላሽ የመስጠት እድልን ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ወይም ለሌላ የህዝብ ኤጀንሲ መስጠት፤ ይህም ቢያንስ የሚከተሉትን ያካትላል:- (ሀ) በኤጀንሲው ምርጫ፡ ቅሬታውን ለመፍታት የቀረበ ሀሳብ፤ **<u>እና</u>** (ለ) ቅሬታ ላቀረበ ወላጅ እና ድርጅቱ በፈቃደኝነት በሽምግልና ለመሳተፍ ለመስማማት እድል መስጠትን ጨምሮ ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ወይም ለሌላ የህዝብ ድርጅት ለቅሬታው ምላሽ እንዲሰጡ እድል መስጠት፤
4. ሁሉንም ተያያዥ መረጃዎችን ይገምግሙ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ወይም ሌላ የህዝብ ድርጅት የ IDEA ክፍል ለ መስፈርቶችን እየጣሰ መሆኑን ገለልተኛ ውሳኔ መወሰን፤ **<u>እና</u>**
5. (ሀ) የእውነታ ግኝቶች እና ማጠቃለያዎች፤ **<u>እና</u>** (ለ) የ SEA የመጨረሻ ውሳኔ ምክንያቶች አስመልክቶ ለቅሬታ አቅራቢው እያንዳንዱን ክስ በሚመለከት የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት።

### የጊዜ መራዘም፤ የመጨረሻ ውሳኔ፤ ትግበራ

ከላይ የተገለጹት የግዛት የትምህርት ድርጅት ሂደቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው:-

1. የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሉ ብቻ፡ የ 60 የቀን መቁጠሪያ የጊዜ ገደብ እንዲራዘም መፍቀድ:- (ሀ) ከልዩ ግዛት ቅሬታ ጋር በተያያዘ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉ፤ **<u>ወይም</u>** (ለ) እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ወይም ሌላ የህዝብ ኤጀንሲ ጉዳዩን በሽምግልና ለመፍታት ጊዜውን ለማራዘም በፈቃደኝነት ከተስማሙ።
2. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ የ SEA የመጨረሻ ውሳኔን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ሂደቶችን ያካትቱ:- (ሀ) የቴክኒክ ድጋፍ ተግባራትን፤ (ለ) ድርድሮች፤ **<u>እና</u>** (ሐ) የህግ ተገዢነትን ለማሳካት የማስተካከያ

እርምጃዎች።

**የግዛት ቅሬታዎች እና ተገቢ የሆኑ የችሎት ሂደቶች**

***ተገቢ የሆነ የቅሬታ አሰራር ሂደት ማቅረብ***፡ በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ላይም ጉዳይ የሆነ የተጻፈ ቅሬታ ከተቀበለ፣ ወይም የግዛቱ ቅሬታ አንድ ወይም ብዙ የዚህ አይነት የችሎት ሂደት አካል የሆኑባቸው በርካታ ጉዳዮችን ከያዘ፣ ግዛቱ የችሎት ሂደቱ እስከሚያልቅ ድረስ ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ውስጥ እየታየ ያለውን ማንኛውንም የአቤቱታ ክፍል ማቆም አለበት። በግዛቱ ውስጥ ያለ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት አካል ያልሆነ ማንኛውም ጉዳይ ከላይ የተገለጸውን የጊዜ ገደብን እና ሂደቶችን በመጠቀም መፍትሄ ማግኘት አለበት።

በግዛት ቅሬታ ላይ የተነሳው ጉዳይ ከዚህ ቀደም ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ውስጥ ተመሳሳይ ወገኖቹን በማሳተፍ (ለምሳሌ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) ውሳኔ ከተሰጥቶ ከነበረ፣ ተገቢ የሆነው የችሎት ሂደት ውሳኔ በዚህ ጉዳይ ላይ አስገዳጅ ነው እና SEA ውሳኔው አስገዳጅ መሆኑን ለቅሬታ አቅራቢውን ማሳወቅ አለበት።

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ውሳኔን ተግባራዊ ባለማድረጋቸው የትምህርት ቤት ዲስትሪክትን ወይም ሌላ የህዝብ ድርጅትን የሚከስ ቅሬታ በ SEA መፍትሄ ማግኘት አለበት።

## የግዛት ቅሬታ ማቅረብ

አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከላይ በተገለጹት ሂደቶች መሰረት የተፈረነበት በጽሁፍ የቀረበ የግዛት ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል። የግዛቱ ቅሬታ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ወይም ሌላ የህዝብ ድርጅት የ IDEA ክፍል ለ መስፈርቶችን ወይም በ 34 CFR ክፍል 300 ውስጥ ያሉትን የአፈፃፀሙን ደንቦች እንደጣሰ የሚያሳይ መግለጫ፤
2. መግለጫው የተመሰረተባቸው እውነታዎች፤
3. ቅሬታውን ያቀረበው ቡድን ፊርማ እና የእውቂያ መረጃ፤ እና
4. አንድ የተወሰነ ልጅን በተመለከተ በሕግ ጥሰቶችን ከተከሰሱ፡-
    (a) የልጁ ስም እና የልጁ የመኖሪያ አድራሻ፤
    (b) ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፤
    (c) ጉዳዩ ስለ ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ከሆነ፣ ለልጁ የሚገኝበት የእውቂያ መረጃ፣ እና ልጁ የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም፤
    (d) ከችግሩ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ፣ የልጁን የችግር ሁኔታ መግለጫ፤ **<u>እና</u>**
    (e) ቅሬታው በሚቀርብበት ጊዜ ቅሬታውን ባቀረበው ቡድን በታወቀው እና በቀረበው መጠን ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የቀረበው ሃሳብ።

ቅሬታው ***በግዛት ቅሬታ አሰራር ሂደቶች አቀባበል*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው ቅሬታው ከተከሰተበት ቀን በፊት ከአንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመውን ጥሰት መክሰስ አለበት።

የግዛቱን ቅሬታ የሚያቀርበው ቡድን ቅሬታውን ለ SEA በሚያቀርብበት ተመሳሳይ ጊዜ ልጁን ለሚያገለግልው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ወይም ሌላ የህዝብ ድርጅት የቅሬታውን ቅጂ መላክ አለበት።

# ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት አሰራሮች

## ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ማቅረብ

**አጠቃላይ**

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም ትምህርታዊ ምደባ፣ ወይም ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን ለመጀመር ወይም ለመቀየር ከቀረበ ሃሳብ ወይም ተቀባይነት አለማግኘት ጋር በተያያዘ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት መጠየቅ ይችላሉ።

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ቅሬታ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት መሰረት ስለሆነው ክስ የቀረበበት ድርጊት ካወቁ ወይም ማወቅ ከነበረብዎት ከሁለት አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ጥሰትን መመክሰስ አለበት።

በጊዜ ቅደም ተከተሉ ውስጥ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ካልቻሉ ከላይ ያለውን የጊዜ ቅደም ተከተል እርስዎን አይመለከትም ምክንያቱም፡-

1. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በተለይ በቅሬታው ውስጥ የተለዩት ጉዳዮች መፍትሄ ማግኘታቸውን በተሳሳተ መንገድ ገልጿል፤ **<u>ወይም</u>**
2. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ለእርስዎ እንዲሰጥ የሚያዘውን መረጃ ከልክሎታል።

**ለወላጆች መረጃ**

ODE መረጃውን ከጠየቁ በአካባቢው የሚገኙ ማንኛውንም ነጻ ወይም በአነስተኛ ዋጋ የሚገኙ ህጋዊ እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያሳውቅዎታል። እርስዎ ከጠየቁ ወይም እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ካቀረቡ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እንዲህ አይነት መረጃ መስጠት አለበት።

## ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት

**አጠቃላይ**

ችሎት ለመጠየቅ፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት (ወይም ጠበቃዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ጠበቃ) ለሌላኛው ቡድን ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማቅረብ አለባችሁ። የችሎቱ ጥያቄ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁሉንም ይዘቶች መያዝ እና ሚስጥራዊ መሆን አለበት።

እንዲሁም ቅሬታውን ያቀረበው ማንኛውም ሰው የችሎት ሂደት ጥያቄውን ቅጂ ለ SEA ማቅረብ አለበት።

**የችሎት ሂደት ጥያቄው ይዘት**

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1. የልጁን ስም፤
2. የልጁን የመኖሪያ አድራሻ፤
3. የልጁን ትምህርት ቤት ስም፤
4. ልጁ የቤት እጦት እያጋጠመው ከሆነ፣ የልጁን የእውቂያ መረጃ እና የልጁን ትምህርት ቤት ስም፤
5. ከችግሩ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ፣ ከታቀደው ወይም ውድቅ ከተደረገው ድርጊት ጋር የተያያዘ የልጁ የችግር ሁኔታ መግለጫ፤ **<u>እና</u>**
6. ለቅሬታ አቅራቢው ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት) በወቅቱ በታወቀው እና በቀረበው መጠን ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የቀረበው ሃሳብ።

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት (ወይም ጠበቃዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ጠበቃ) ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ያካተተ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ እስኪሚያቀርቡ ድረስ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ላይኖራችሁ ይችላል።

### የችሎት ሂደት ጥያቄ በቂነት

የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ወደ ፊት እንዲሄድ፣ በቂ እንደሆነ መታሰብ አለበት። የችሎት ጥያቄው የተቀበለው ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ወረዳ) ቅሬታው በደረሰው በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ተቀባዩ አካል የችሎቱ ጥያቄ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን አለማሟላቱን እንደሚያምን ለችሎቱ መኮንን እና ለሌላኛው ቡድን፣ በጽሁፍ ካላሳወቁ በስተቀር የችሎት ጥያቄው በቂ እንደሆነ (ከላይ ያሉትን የይዘት መስፈርቶች እንዳሟላ) ይቆጠራል።

ተቀባዩ ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት በቂ እንዳልሆነ የሚያሳየው ማስታወቂያ በደረሰው በአምስት የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ የችሎት መኮንኑ ቅሬታው ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን መወሰን፣ እና ወዲያውኑ ለእርስዎ እና ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

### የችሎት ሂደት ጥያቄ ማሻሻያ

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በችሎቱ ጥያቄ ላይ ለውጦችን ማድረግ የሚችሉት የሚከተሉት ከሆኑ ብቻ ነው፡-

1. ሌላኛው ቡድን ለውጦቹን በጽሁፍ ካረጋገጠ እና ***የመፍትሄ ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ ተገቢ የሆነ ችሎት ሂደት ጥያቄውን በመፍትሄ ስብሰባ ለመፍታት እድል ከተሰጠው፤ ***ወይ***
2. ተገቢ የሆነ ችሎት ሂደቱ ከመጀመሩ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ የችሎት መኮንኑ ለለውጦቹ ፈቃድ ከሰጠ።

ቅሬታው አቅራቢው ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) በተገቢ የሆነ ችሎት ሂደት ጥያቄ ላይ ለውጦች ካደረጉ፣ ለመፍትሄ ስብሰባው የጊዜ ቅደም ተከተሎች (የችሎቱ ጥያቄ በደረሰው በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) እና ለመፍትሄው ጊዜ (የችሎቱ ጥያቄ በደረሰው በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) የተሻሻለው ቅሬታ በቀረበበት ቀን እንደገና ይጀምራል።

### ተገቢ ለሆነ የቅሬታ ሂደት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ምላሽ

***በቀዳሚ የጽሁፍ ማስታወቂያ***: ስር እንደተገለጸው፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደትዎ ውስጥ ያለውን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ፣ ቀዳሚ የጽሁፍ ማስታወቂያ ካልላክለልዎት፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ በደረሰው በ10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ የሚከተለውን የሚያካትት ምላሽ መላክ አለበት፡-

1. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደት ላይ የተነሳውን ተግባር ለምን እንዳቀረበ ወይም ድቅ እንዳደረገ ማብራሪያ፤
2. የልጅዎ የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ግምት ውስጥ ያስገባቸው የሌሎች አማራጮች መግለጫ እና እነዚያ አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸው ምክንያቶች፤
3. የእያንዳንዱ ግምገማ ሂደት፣ ግምገማ፣ መዝገብ፣ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለታቀደው ወይም ውድቅ ለተደረገው ተግባር እንደ መሰረት ያተጠቀመበት ሪፖርት መግለጫ፤ <u>**እና**</u>
4. በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ከታቀደው ወይም ውድቅ ከተደረገው ተግባር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ።

ከላይ ከቁጥር 1-4 ባሉት ውስጥ ያለውን መረጃ መስጠት የትምህርት ዲስትሪክቱ ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄዎ በቂ እንዳልነበረ ከመግለጽ አያግደውም።

### ተገቢ ለሆነ የቅሬታ ሂደት የሌላ ቡድን ምላሽ

ከላይ ***ተገቢ ለሆነ የቅሬታ ሂደት የትምህርት ቤት ዲሰሪክት ምላሽ***: በሚለው፣ ንዑስ ርዕስ ስር ከተገለጸው በስተቀር፣ ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ የሚቀበለው ቡድን፣ የችሎት ጥያቄው በደረሰው 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ለሌላኛው ቡድን በችሎት ጥያቄ ውስጥ ያሉ ጉዳዮች የተለየ ምላሽ የሚሰጥ ምላሽ መላክ አለበት።

## የሞዴል ቅጾች

SEA ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ እንዲያቀርቡ እና እርስዎ እና ሌሎች ቡድኖች የግዛት ቅሬታ እንዲያቀርቡ ለመርዳት ሞዴል ቅጾችን ማዘጋጀት አለበት። ይሁን እንጂ፣ የእርስዎ ግዛት ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እነዚህን የሞዴል ቅጾች መጠቀም ላያስፈልጋቸው ይችላል። በእርግጥ፣ ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄን ወይም የግዛት ቅሬታን ለማቅረብ አስፈላጊውን መረጃ እስከያዘ ድረስ የግዛቱን ሞዴል ቅጾች ወይም ሌላ ተስማሚ ቅጽ መጠቀም ይችላሉ።

## ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት እና የችሎት ሂደት በመጠባበቅ ላይ እያለ፡ የልጁ ምደባ

***አካል ጉዳተኛ ልጆችን ቅጣት በሚቀበሉበት ጊዜ የሚደረጉ የአሰራር ሂደቶች፡*** በሚለው ርዕስ ስር ከቀረበው በስተቀር፣ አንድ ጊዜ ለሌላኛው ቡድን ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ከተላከ፣ በመፍትሄው ሂደት፣ እና ለማንኛውም ገለልተኛ ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔን በሚጠባበቁበት ወቅት፣ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር፣ ልጅዎ አሁን ባለው የትምህርት ምደባ ውስጥ መቆየት አለበት። ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደት ለህዝብ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቅበላ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጅዎ፣ በእርስዎ ፈቃድ፣ እነዚህ ሂደቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በመደበኛ የህዝብ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መመደብ አለበት።

ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደት ለህዝብ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቅበላ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጅዎ በእርስዎ ፈቃድ፣ እነዚህ ሂደቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በመደበኛ የህዝብ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መመደብ አለበት።

ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደቱ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት በIDEA ክፍል ሐ አገልግሎት ከማግኘት ወደ ለክፍል ለ የተሸጋገረ ልጅ እና ሶስት አመት ስለሞላው ለክፍል ሐ አገልግሎቶች ከዚህ በኋላ ብቁ ለማይሆን ልጅ ለመጀመሪያ አገልግሎቶችን ማመልከቻ የሚያካትት ከሆነ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጁ ሲገኝ የነበረውን ክፍል ሐ አገልግሎቶች እንዲሰጥ አይገደድም። ልጁ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አፈልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያገኝ ከፈቀዱ፣ የችሎት  ሂደቱን ውጤት በመጠባበቁበት ጊዜ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በክርክር ውስጥ የሌሉትን (እነዚያ ሁለታችሁም እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የተስማማችሁባቸው) እነዚያን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት። በግዛቱ የትምህርት ድርጅት በተካሄደው ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ውስጥ ያለ አንድ የችሎት መኮንን የምደባ ለውጥ ተገቢ እንደሆነ ከእርስዎ ጋር ከተስማማ፣ ምደባው ልጅዎ ማንኛውንም ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ሲጠብቅ የሚቆይበት እንደ የልጅዎ የአሁን ትምህርት ምደባ ተደርጎ መታየት አለበት።

## *የመፍትሄ ሂደት*

### የመፍትሔ ስብሰባ

ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደትዎ ማስታወቂያ በደረስዎ በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ እና ተገቢ የሆነው የችሎት ሂደት ከመጀመሩ በፊት፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ከእርስዎ እና ከሚመለከተው አባል ወይም ተገቢ የሆነው የቅሬታ ሂደት ውስጥ ስለተለዩት እውነታዎች ልዩ እውቀት ካላቸው የግለሰብ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት ጋር ስብሰባ መጥራት አለበት።  ስብሰባው፡-

1. የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱን ወክሎ የመወሰን ስልጣን ያለው የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተወካይ ማካተት አለበት፤ <u>**እና**</u>
2. ከጠበቃ ጋር ካልሄዱ በስተቀር የትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት ጠበቃ ላያካትት ይችላል።

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በስብሰባው ላይ ለመሳተፍ የሚመለከታቸውን የ IEP ቡድን አባላት ይወስናሉ።

የስብሰባው አላማ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄዎን፣ እና የጥያቄው መሰረት በሆኑት እውነታዎች ላይ ለመወያየት ነው፣ ይህም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት አለመግባባቱን ለመፍታት እድል እንዲኖረው ነው።

በሚከተሉት ምክንያት የመፍትሄ ስብሰባው አስፈላጊ አይሆንም፡-

1. እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ስብሰባውን ለመተው በጽሁፍ ከተስማሙ፤ <u>***ወይም***</u>
2. እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ***ሽምግልና*** በሚለው ርእስ ስር እንደተገለጸው የሽምግልና ሂደቱን ለመጠቀም ከተስማሙ።

### የመፍትሄ ጊዜ

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክትተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄው በደረሰው በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ እርሶን በሚያረካ መልኩ መፍትሄ ካልሰጠ (በመፍትሄው ሂደት ጊዜ)፣ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ሊደረግ ይችላል።

የመጨረሻ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ውሳኔ ለመስጠት የ45 ቀን የቀን መቁጠሪያ የጊዜ ቅደም ተከተሉ፣ ***የችሎት ውሳኔዎች፡*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ የሚጀምረው ለ30 የቀን መቁጠሪያ ቀኑ ላይ ከተደረጉት ማስተካከያዎች በስተቀር፣ ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣የ30 ቀን የመፍትሄ ጊዜ ሲያበቃ ነው።

ሁለታችሁም እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የመፍትሄ ሂደቱን ለመተው ወይም ሽምግልናን ለመጠቀም ካልተስማሙ በስተቀር፣ ስብሰባው እስኪደረግ ድረስ በመፍትሄው ስብሰባ ላይ አለመሳተፍዎ የመፍትሄ ሂደቱን እና ተገቢ የሆነ የችሎት

ሂደቱን የጊዜ ቅደም ተከተል ያዘገየዋል።

ተገቢ የሆኑ ጥረቶችን ካላደረጉ እና እነዚህን ጥረቶች ከመዘገበ በኋላ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በመፍትሄ ስብሰባው ላይ የእርስዎን ተሳትፎ ማግኘት ካልቻለ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በ30 የቀን አቆጣጠር ውስጥ የመፍትሄ ጊዜ ማብቂያ ላይ፣ ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት የጠየቀው ጥያቄ እንዲሰርዝ የችሎት መኮንኑን ሊጠይቅ ይችላል። ለእንደዚህ አይነት ጥረቶች ማስረጃዎች የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ጊዜ ያደረጋቸን ሙከራዎች የጊዜ እና ቦታ መዝገብ ማካተት አለበት፣ ለምሳሌ፡-

1. የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች እና የእነዚያን ጥሪዎች ውጤቶች ዝርዝር መዛግብት፤
2. ወደ እርስዎ የተላኩ የደብዳቤ ቅጂዎች እና የተቀበሉት ምላሾች፤ **<u>እና</u>**
3. ወደ ቤትዎ ወይም ወደ ስራ ቦታዎ የተደረጉ ጉብኝቶች እና የእነዚያ ጉብኝቶች ውጤቶች ዝርዝር መዛግብት።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የእርስዎ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማስታወቂያ በደረሰው በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ስብሰባውን ማካሄድ ካልቻለ **<u>ወይም</u>** የመፍትሄ ስብሰባው ላይ ካልተሳተፈ፣ የ45 የቀን መቁጠሪያ ቀን ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት የጊዜ ደም ተከተል እንዲጀምር የችሎት መኮንኑን መጠየቅ ይችላሉ።

### የ 30 የቀን መቁጠሪያ ቀን መፍትሄ ጊዜ ማስተካከያዎች

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የመፍትሄውን ስብሰባ ለመተው በጽሁፍ ከተስማሙ፣ የ45 የቀን መቁጠሪያ ቀን ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት የጊዜ ቅደም ተከተል በሚቀጥለው ቀን ይጀመራል።

ሽምግልና ወይም የመፍትሄ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ እና የ30 የቀን መቁጠሪያ ቀን የመፍትሄ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት፣ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ምንም አይነት ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በጽሁፍ ከተስማሙ፣ ተገቢ ለሆነው የችሎት ሂደት የ45 የቀን መቁጠሪያ ቀን የጊዜ ቅደም ተከተል በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የሽምግልና ሂደቱን ለመጠቀም ከተስማሙ ነገር ግን እስካሁን ስምምነት ላይ ካልደረሱ፣ በ30 ቀን መቁጠሪያው የመፍትሄ ጊዜ ማብቂያ ላይ ሁለቱም ወገኖች በሂደቱ ለመቀጠል በጽሁፍ ከተስማሙ የሽምግልና ሂደቱ ሊቀጥል ይችላል። ይሁን እንጂ፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በዚህ በቀጠለው ጊዜ ከሽምግልና ሂደት ከወጡ፣ የ45 ቀን መቁጠሪያው ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት የጊዜ ቅደም ተከተል በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

### በጽሑፍ የቀረበ ስምምነት

በመፍትሄው ስብሰባ ላይ አለመግባባቱን ለመፍታት ከተወሰነ፣ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ህጋዊ አስገዳጅ ስምምነት ማድረግ አለባቹ ይህም፡-

1. በእርስዎ እና ትምህርት ቤቱን ዲስትሪክት የማስገደድ ስልጣን ባለው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ተወካይ፤ **<u>እና</u>**
2. በማንኛውም የግዛት ፍርድ ቤት ብቁ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት (ይህንን አይነት ጉዳይ ችሎት የመስጠት ስልጣን ያለው የግዛት ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ተፈጻሚ ይሆናል።

### የስምምነት ግምገማ ጊዜ

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በመፍትሄ ስብሰባ ምክንያት ወደ ስምምነት ከገባችሁ፣ ከሁለት አንዳችሁ (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ሁለታችሁም ስምምነቱን ከፈረማችሁበት ጊዜ አንስቶ ባሉት 3 የስራ ቀናት ውስጥ ስምምነቱን ሊያፈርሱ ይችላሉ።

# ተገቢ በሆነ የቅሬታዎች ሂደት ላይ የሚደረጉ ችሎቶች

## ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት

**አጠቃላይ**

በማንኛውም ጊዜ ተገቢ የሆነ ችሎት ሂደት በሚጠየቅበት ጊዜ፣ ***ተገቢ በሆነ የቅሬታ ሂደት*** እና ***የመፍትሄ ሂደት*** ክፍሎች ውስጥ እንደተገለጸው፣ በክርክሩ ውስጥ የተሳተፉት እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክሪት ለገለልተኛ ተገቢ የሆነ ችሎት ሂደት እድል ሊኖራችሁ ይገባል።

**ገለልተኛ የችሎት ሂደት መኮንን**

ቢያንስ፣ የችሎት ሂደት መኮንኑ፦

1. በልጁ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ውስጥ የተሳተፈ የ SEA ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኛ መሆን የለበትም። ይሁን እንጂ፣ አንድ ሰው የድርጅቱ ተቀጣሪ አይደለም ምክንያቱም ግለሰቡ በ ODE ድርጅት የሚከፈለው እንደ ችሎት ሂደት መኮንን ሆኖ እንዲያገለግል ነው፤
2. በችሎቱ ውስጥ ካለው ከ ALJ ፍርድ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም ሙያዊ ጥቅም ሊኖረው አይገባም፤
3. እውቀት ያለው እና የIDEA አቅርቦቶችን እና ከ IDEA ጋር ግንኙነት ያላቸው በፌደራል እና በግዛት ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የህግ ትርጓሜዎችን መረዳት አለበት፤ <u>**እና**</u>
4. ከተገቢው መደበኛ የህግ አሰራር ጋር የሚጣጣሙ፣ ችሎቶችን ለማካሄድ፣ እና ውሳኔዎችን ለመወሰን እና ለመጻፍ እውቀት እና ችሎታ ሊኖረው ይገባል።

እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እንደ ALJዎች የሚያገለግሉት ሰዎች ዝርዝር እና የእያንዳንዱን የብቃት መግለጫ መያዝ አለበት።

**ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ርዕሰ ጉዳይ**

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት የጠየቀው ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) ሌላኛው ወገን ካልተስማም በስተቀር፣ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ማንሳት አይችሉም።

**ችሎት ለመጠየቅ የጊዜ ቅደም ተከተል**

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በችሎት ጥያቄ ውስጥ ስለ ቀረበው ጉዳዩ(ዎች) ካወቁበት ወይም ማወቅ ከነበረብዎት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት አመታት እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ላይ ገለልተኛ ችሎት መጠየቅ አለብዎት።

**ለጊዜ ቅደም ተከተሉ የተለዩ ሁኔታዎች**

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማቅረብ ካልቻሉ ከላይ ያለው የጊዜ ሰሌዳ እርስዎን አይመለከትም ምክንያቱም፦

1. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እርስዎ በቅሬታዎ ላይ ያነሱትን ችግር ወይም ችግር እንደተፈታ በተለየ መልኩ አሳስቶታል፤ <u>**ወይም**</u>
2. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ለእርስዎ እንዲሰጥዎ የታዘዘውን መረጃ አልሰጠዎትም።

## የችሎት ሂደት መብቶች

### አጠቃላይ

ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ላይ እራስዎን የመወከል መብት አለዎት። በተጨማሪ፣ ማንኛውም ቡድን ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት (ከቅጣት ሂደቶች ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ) የሚከተሉትን የማድረግ መብት አለው፡-

1. የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ችግር በተመለከተ ከጠበቃ እና/ወይም ልዩ እውቀት ወይም ስልጠና ካላቸው ሰዎች ጋር አብሮ የመሆን እና ምክር የማግኘት፤
2. ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ላይ በጠበቃ መወከል፤
3. ማስረጃ ማቅረብ እና የመግጠም፣ ምስክርን የመጠየቅ እና ምስክሮች እንዲገኙ መጠየቅ፤
4. ችሎቱ ከመካሄዱ አምስት የስራ ቀናት በፊት ለቡድኑ ያልገለጸውን ማንኛውንም ማስረጃ በችሎቱ ላይ ማስተዋወቅን መከልከል፤
5. ችሎቱን በጽሁፍ፣ ወይም፣ በምርጫዎ፣ በኤሌክትሮኒክ፣ የቃል ለቃል መዝገብ ማግኘት፤ **<u>እና</u>**
6. በጽሁፍ፣ ወይም፣ በምርጫዎ ኤሌክትሮኒካዊ የእውነታ ግኝቶችን እና ውሳኔዎችን ያግኙ።

### መረጃን ይፋ የማድረግ ተጨማሪ መግለጫ

ተገቢ ከሆነ የችሎት ሂደት ከመጀመሩ ቢያንስ ከአምስት የስራ ቀናት በፊት፣ እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በዚያ ቀን ያጠናቀቁትን ሁሉንም ግምገማዎች እና በእነዚያ ግምገማዎች መሰረት እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በችሎቱ ላይ ሊጠቀሙባቸው ባሰቧቸው ምክረ ሃሳቦች ላይ እርስ በእርስ ይፋ ማድረግ አለባችሁ።

የችሎቱ መኮንን ይህንን መስፈርት ያላሟላ ማንኛውም ቡድን ከሌላኛው ወገን ፈቃድ ውጪ ተያያዥ ግምገማ ወይም ምክረ ሃሳብ በችሎቱ ላይ እንዳያቀርብ ሊከለክል ይችላል።

### በችሎት ሂደቶች ላይ የወላጅ መብቶች

የሚከተሉትን ለማድረግ መብት ሊሰጥዎት ይገባል፡-

1. በችሎት ሂደት ላይ ልጅዎን እንዲገኝ ማድረግ፤
2. የችሎቱ ሂደቱን ለህዝብ ክፍት ማድረግ፤ **<u>እና</u>**
3. የችሎቱን፣ የእውነታውን ግኝቶች እና ውሳኔዎች መዝገብ ያለ ምንም ክፍያ ለእርስዎ መስጠት።

## የችሎት ሂደት ውሳኔዎች

### የአስተዳደር ህግ ዳኛ ውሳኔ

የችሎት መኮንን ልጅዎ ነጻ ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ማግኘቱን ወይም አለማግኘቱን በተመለከተ ሚሰጠው ውሳኔ ከ FAPE ጋር በቀጥታ በተያያዙ ማስረጃዎች እና ክርክሮች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

የአሰራር ሂደት ጥሰት ላይ ክስ በሚያቀርቡ ጉዳዮች ላይ (ለምሳሌ “ያልተሟላ የ IEP ቡድን”)፣ የሚከተሉት የአሰራር ሂደት ጥሰቶች የችሎት መኮንኑ ልጅዎ ያልተቀበለው FAPE ብቻ እንደሆነ ሊያውቅ ይችላል፡-

1. በልጅዎ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) መብት ላይ ጣልቃ ከገባ፤
2. ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን በሚመለከት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድልዎ ላይ ጉልህ በሆነ መልኩ ጣልቃ ሲገባ፤ ***<u>ወይም</u>***
3. የልጅዎን ትምህርታዊ ጥቅማጥቅሞች እንዲከለከል ሲያደርግ።

ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዳቸውም የችሎት መኮንኑበIDEA ክፍል ለ (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) ስር ባለው የፌደራል ደንቦች የአሰራር ሂደት ጥበቃ ክፍል ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች እንዲያከብር የትምህርት ቤት ዲስትሪክትን እንዲያዝ ለመከላከል ሊተረጎሙ አይችሉም።

### ተገቢ ለሆነ የችሎት ሂደት የተለየ ጥያቄ

በ IDEA ክፍል ለ (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) ስር ባለው የፌደራል ደንቦች የስራር ሂደት ጥበቃ ክፍል ውስጥ ቀደም ሲል ከቀረበ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት የተለየ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ከማቅረብ በሚከለክል ምንም ነገር ሊተረጎም አይችልም።

### ለአማካሪ ፓነል እና ለአጠቃላይ ህዝብ የቀረቡ ግኝቶች እና ውሳኔዎች

SEA ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ (ለችሎትዎ ሃላፊነት ያለው (የትኛውም ሃላፊነት ያለው)፣ በግል የሚለይ መረጃ ከሰረዘ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

1. ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ውስጥ የተገኙትን ግኝቶችን እና ውሳኔዎች ማቅረብ ወይም ለግዛቱ ልዩ ትምህርት አማካሪ ፓናል ይግባኝ መጠየቅ፤ **እና**

2. እነዚያን ግኝቶች እና ውሳኔዎች ለህዝብ ተደራሽ ያድርጉ።

## የችሎት ሂደት ቅደም ተከተሎች እና አመቺነት፤ የመጨረሻ ውሳኔ

SEA 30 የቀን መቁጠሪያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመፍትሄ ስብሰባዎች፣ **ወይም**፡ በንዑስ ርዕስ ስር እንደተገለጸው ***30 የቀን መቁጠሪያ መፍትሄ ጊዜ ማስተካከያዎች፣*** የተስተካከለው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከ45 የቀን መቁጠሪያ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

1. በችሎቱ የመጨረሻ ውሳኔ መድረሱን፤ **እና**

2. የውሳኔው ቅጂ ለእያንዳንዱ ቡድኖች በፖስታ መላኩን።

የችሎት መኮንኑ ከሁለት አንዱ ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) ጥያቄ ከላይ ከተገለጸው የ45 ቀን መቁጠሪያ ጊዜ በላይ የተለየ የጊዜ ማራዘሚያዎች ሊሰጥ ይችላል።

እያንዳንዱ ችሎት ለእርስዎ እና ለልጅዎ ተገቢ በሆነ ምቹ ጊዜ እና ቦታ መከናወን አለበት።

### የመጨረሻ የችሎት ሂደት ውሳኔ

ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ላይ የተሰጠው ውሳኔ (ከቅጣት ሂደቶች ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ)፣ በችሎቱ ውስጥ ከተሳተፈ ማንኛውም አካል (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትርክት)፣ ***የሲቪል ተግባራት፣ እነዚያን ድርጊቶች የሚያቀርቡበትን ጊዜ ጨምሮ*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ የሲቪል ተግባር በማምጣት ይግባኝ ካልጠየ በስተቀር የመጨረሻ ነው።

## የሲቪል ተግባራት፣ እነዚያን ተግባራት የሚያቀርቡበትን ጊዜ ጨምሮ

### አጠቃላይ

ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ግኝቶች እና ውሳኔዎች (ከቅጣት ሂደቶች ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ) ያልተስማማ ማንኛውም ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ርዕሰ ጉዳዩ የሆነውን ጉዳይ በተመለከተ ላይ የሲቪል ተግባር የማቅረብ መብት አለው።  ተግባሩ በግዛት ፍርድ ቤት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት (እንደዚህ አይነት ጉዳይ ላይ ችሎት የመስጠት ስልጣን ያለው የክልል ፍርድ ቤት) ወይም በፌደራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ክርክር ውስጥ ያለውን መጠን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ሊቀርብ ይችላል።

### የጊዜ ገደብ

ተግባሩን የሚያመጣው ቡድን (እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት) የሲቪል ተግባር ለማቅረብ የችሎቱ መኮንን ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ 90 የቀን መቁጠሪያ ቀናት አለው።

### ተጨማሪ ሂደቶች

በማንኛውም የሲቪል ተግባር፣ ፍርድ ቤቱ፡-

1. የአስተዳደር ሂደቶች መዝገቦችን ይቀበላል፤

2. በእርስዎ ጥያቄ ወይም በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፤ **እና**

3. ውሳኔውን በማስረጃው ጠቀሜታ መጠን ላይ በመመስረት ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ የወሰነውን እርዳታ ይሰጣል።

አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች፣ የዳኝነት እርዳታ የግል ትምህርት ቤት ክፍያ እና የማካካሻ ትምህርት አገልግሎቶች ማወራረጃን ሊያካትት ይችላል።

### የዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች ስልጣን

የዩናይትድ ስቴትስ የዲትሪክት ፍርድ ቤቶች በ IDEA ክፍል ለ ስር በተከሰቱት ድርጊቶች ላይ የክርክር መጠንን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ የመወሰን ስልጣን አላቸው።

### የአሰራር ደንብ

በእነዚህ ህጎች መሰረት የሲቪል ተግባሩ ከመቅረቡ በፊት በ IDEA ክፍል ለ ስር የሚገኝነውም እርዳታ ካልፈለገ በስተቀር፣ በ IDEA ክፍል ለ ውስጥ ምንም ነገር በ U.S. ህገ መንግስት ስር ያሉ፣ የ1990 የአሜሪካ አካል ጉዳተኞች ህግ፣ የ1973 የመልሶ ማቋቋም አዋጅ ርዕስ V (ክፍል 504)፣ ወይም ሌሎች አካል ጉዳተኛ ልጆችን ሙብቶችን የሚጠብቁ የፌደራል ሙብቶችን፣ ሂደቶችን እና መፍትሄዎችን አይከለክልም ወይም አይገድብም፣ ከላይ የተገለጹት ተገቢ የሆኑ የአሰራር ሂደቶች ቡድኑ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ተግባሩን ካቀረበ በሚፈለገው መጠን መጠናቀቅ አለባቸው። ይህ ማለት በ IDEA ስር ከሚገኙት ጋር በተደራረቡ ሌሎች ህጎች ስር የሚገኙ መፍትሄዎች ሊኖሩዎት ይችላል፣ ነገር ግን፣ በአጠቃላይ፣በእነዚያ በሌሎች ህጎች እርዳታ ለማግኘት፣ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት በመጀመሪያ በ IDEA ስር ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች መጠቀም አለብዎት (ማለትም፣ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት፤ መፍትሄው ስብሰባን ጨምሮ፣ የመፍትሄ ሂደት፤ እና ገለልተኛ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደቶችን ጨምሮ)።

## የጠበቃዎች ክፍያዎች

### አጠቃላይ

በ IDEA ክፍል ለ ስር በቀረበ ማንኛውም ተግባር ወይም ሂደት፣ ድል ካገኙ (ካሸነፉ)፣ ፍርድ ቤቱ፣ በራሱ ውሳኔ፣ ለእርስዎ እንደ የወጪ አካል ምክንያታዊ የሆነ የጠበቆች ክፍያን ሊሰጥዎ ይችላል።

በ IDEA ክፍል ለ ስር በቀረበ ማንኛውም ተግባር ወይም ሂደት፣ ፍርድ ቤቱ፣ በራሱ ውሳኔ፣ እንደ ወጪው የግዛት ትምህርት ድርጅት አካል ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ለጠበቃዎ የሚከፍሉትን፣ ምክንያታዊ የሆነ የጠበቆች ክፍያዎችን ሊሰጥ ይችላል፣ ጠበቃው፦ (ሀ) ፍርድ ቤቱ የማይጠቅም፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሰረት የሌለው ሆኖ ያገኘውን ቅሬታ ወይም የፍርድ ቤት ክስ ካቀረበ፤ **<u>ወይም</u>** (ለ)ሙግቱ የማይጠቅም፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሰረት የሌለው ከሆነ በኋላ ሙግት ከቀጠለ፤ **<u>ወይም</u>**

በ IDEA ክፍል ለ ስር በቀረበ ማንኛውም ተግባር ወይም ሂደት፣ ጥያቄዎ ተግቢ የሆነ የችሎት ሂደት ወይም ቀጥሎ ለሚደረግ የፍርድ ቤት ጉዳይ ለማንኛውም ተገቢ ላልሆነ አላማ፣ ለምሳሌ ለጥቃት፣ አላስፈላጊ መዘግየትን ለማምጣት፣ ወይም ለተግባሩን ወይም የችሎት ሂደቱን ወጪ ሳያስፈልግ ለመጨመር ከቀረበ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ፣ ምክንያታዊ የሆኑ የጠበዎች ክፍያዎችን ለከፍተኛ የግዛት ትምህርት ድርጅት ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እንደ ወጪ አካል፣ በእርስዎ ወይም በጠበቃዎ ሊከፍል ይችላል።

### የክፍያዎች ሽልማት

ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆኑ የጠበቆች ክፍያዎችን እንደሚከተለው ይከፍላል፦

1. ክፍያዎች ድርጊቱ ወይም የችሎት ሂደቱ በተከሰተበት ማህበረሰብ ውስጥ ባለው ዋጋ እና ለቀረቡት አገልግሎቶች አይነት እና ጥራት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው። የተሰጡ ክፍያዎችን ሲሰሉ ምንም ጉርሻ ወይም ማባዣ ጥቅም ላይ ላይውል ይችላል።

2. በ IDEA ክፍል ለ መሰረት በማንኛውም ተግባር ወይም የችሎት ሂደት ውስጥ የጽሁፍ ስምምነት ከተሰጠዎት በኋላ ለሚደረጉ አገልግሎቶች በሚከተሉት ምክንያቶች የጠበቃዎች ክፍያ ላይሰጡ እና ተዛማጅ ወጪዎች ላይወራረዱ ይችላሉ፦

    a. ሽልማቱ በፌደራል የፍትሃብሄር ህግ ደንብ 68 በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ወይም ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጉዳይ፣ የችሎት ሂደት ከመጀመሩ ከ10 የቀን መቁጠሪያ በላይ ባለው በማንኛውም ጊዜ ከተሰጠ፤

    b. ሽልማቱ በ10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ካልተቀበሉ፤ **<u>እና</u>**

    c. ፍርድ ቤቱ ወይም የአስተዳደር የችሎት መኮንን በመጨረሻ ያገኙት እርዳታ ከስጦታው ስምምነት የበለጠ ለእርስዎ የማይመች ሆኖ ካገኘው።

    ምንም እንኳን እነዚህ ገደቦች ቢኖሩም፣ ካሸነፉ እና የቀረበውን ስምምነት ውድቅ በማድረግ በጠንካራ መንገድ በቂ ምክንያት ካቀረቡ የጠበቃዎች ክፍያ እና ተዛማጅ ወጪዎች ሽልማት ሊሰጥዎት ይችላል።

3. ስብሰባው የተካሄደው በአስተዳደራዊ የችሎት ሂደት ወይም በፍርድ ቤት ክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከማንኛውም የግለሰብ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ጋር በተያያዘ ክፍያዎች ላይሰጡ ይችላሉ። እንዲሁም ***ሽምግልና*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው ክፍያዎች ለሽምግልና ላይሰጡ ይችላሉ።

የመፍትሄ ስብሰባ፣ ***የመፍሄ ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ በአስተዳደራዊ ችሎት ወይም በፍርድ ቤት ክስ ምክንያት እንደተጠራ ስብሰባ አይቆጠርም፣ እንዲሁም ለእነዚህ ጠበቆች ክፍያዎች አቅርቦቶች አላማ እንደ አስተዳደራዊ ችሎት የሂደት ወይም የፍርድ ቤት ክስ አይቆጠሩም።

ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች፣ በ IDEA ክፍል ለ ስር የሚሰጠውን የጠበቆች ክፍያ መጠን፣ እንደ ተገቢነቱ ይቀንሳል፡-

1. እርስዎ፣ ወይም ጠበቃዎ፣ በድርድሩ ወይም በችሎት ሂደቱ ወቅት፣ የክርክሩን የመጨረሻ መፍትሄ ያለምክንያት ካዘገዩ፤
2. ተመሳሳይ ክህሎት፣ ዝና፣ እና ልምድ ባላቸው ጠበቆች ለሚሰጡ ተመሳሳይ አገልግሎቶች እንዲሰጥ የተፈቀደው የጠበቆች የክፍያ መጠን ያለምክንያት በማህበረሰብ ውስጥ ካለው መደበኛ የሰዐት ክፍያ ከበለጠ ፤
3. የድርጊቱን ወይም የችሎት ሂደቱን ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት የወሰደው ጊዜ እና የቀረቡት የህግ አገልግሎቶች ከመጠን በላይ ከነበሩ፤ ***<u>ወይም</u>***
4. እርስዎን የሚወክለው ጠበቃ ***ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት ጥያቄ ማስታወቂያ ላይ ተገቢውን መረጃ ለትምህርት ቤት ዲስትሪክት ካላቀረበ።

ነገር ግን፣ ፍርድ ቤቱ ግዛቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ያለምክንያት የድርጊቱን ወይም የችሎት ሂደቱን የመጨረሻ ውሳኔ እንዳዘገዩ ወይም በ IDEA ክፍል ለ መሰረት የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች አቅርቦቶች ጥሰት መፈጸሙን ካወቀ ክፍያዎችን ላይቀንስ ይችላል።

# የአካል ጉዳተኛ ልጆች በሚቀጡበት ጊዜ የሚኖሩ የአሰራር ሂደቶች

## የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን

### በእያንዳንዱን ጉዳይ ውሳኔ መስጠት

ከቅጣት ጋር በተገናኘ በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት፣ የትምህርት ቤቱን የተማሪ ስነምግባር ደንብ ለጣሰ አካል ጉዳተኛ ልጅ የምደባ ለውጥ፣ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በሚወስኑበት ጊዜ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች በእያንዳንዱን ጉዳይ ማንኛውንም አይነት ልዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ።

### አጠቃላይ

አካል ጉዳተኛ ላለሆኑ ልጆችም እንዲህ ያለውን እርምጃ በሚወስዱበት መጠን፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ በተከታታይ ከ **10 የትምህርት ቀናት** ላልበለጡ ጊዜያት የተማሪን የስነ ምግባር ደንብ የጣሰ የአካል ጉዳተኛ ልጅን አሁን ካለበት ምደባ ተስማሚ ወደሆኑ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ፣ ሌላ ቦታ ሊያባርሩ፣ ወይም ሊያግዱ ይችላሉ። እንዲሁም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለተለያዩ የስነምግባር ጉድለት ክስተቶች በዚያ ተመሳሳይ የትምህርት ዘመን ውስጥ በተከታታይ ከ **10 የትምህርት ቀናት** ላልበለጡ ጊዜያት፣ እነዚያ ማባረሮች የምደባ ለውጥ እስካላደረጉ ድረስ (ለትርጉሙ ***በማባረር ቅጣት ምክንያት የምደባ ለውጥ*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ) በልጁ ላይ ተጨማሪ ማባረሮችን ሊጥሉ ይችላሉ።

አንድ ጊዜ አካል ጉዳተኛ ልጅ በተመሳሳይ የትምህርት ዘመን በአጠቃላይ ለ **10 የትምህርት ቀናት** አሁን ካለበት ምደባ ከተባረረ፣ የትምህርት ቤቱ ዲትሪክት፣ በዚያ የትምህርት ዘመን ማናቸውም ተከታታይ የተባረረበት ቀናት፣ ***አገልግሎቶች*** በሚለው ንዑስ ርዕስ መሰረት በሚፈለገው መጠን አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።

### ተጨማሪ ስልጣን

የተማሪ የስነምግባር ደንብን የጣሰው ባህሪ የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ ካልሆነ (***የመገለጥ ውሳኔ*** የሚለውን ንዑስ ርእስ ይመልከቱ) እና የምደባ ለውጡ ቅጣት በተከታታይ ከ **10 የትምህርት ቀናት** ከበለጠ፣ ትምህርት ቤቱ ከታች *አገልግሎቶች* በሚለው መሰረት እንደተገለጸው ለልጁ አገልግሎቶችን መስጠቱ የግድ ካልሆነ በስተቀር፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ልጆች እንደሚቀጡት አካል ጉዳተኛ ለሆነው ልጅ በተመሳሳይ መልኩ እና ለተመሳሳይ ጊዜ የቅጣት ሂደቶችን ሊተገብሩ ይችላሉ። የልጁ የ IEP ቡድን ለእንደዚህ አይነት አገልግሎቶች ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታን ይወስናል።

## አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ተመሳሳይ ሁኔታ ለተባረረ አካል ጉዳተኛ ላልሆነ ልጅ አገልግሎቶችን ከሰጠ፣ አሁን ካለበት ምደባ በዚያ የትምህርት ዘመን ለ **10 የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ** ለተባረረ አካል ጉዳተኛ ልጅ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል። አሁን ካለበት ምደባ ለተባረረ አካል ጉዳተኛ ልጅ መስጠት ያለባቸው አገልግሎቶች በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ሊሰጥ ይችላል።

አሁን ካለበት ምደባ **ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ** ለተባረረ አካል ጉዳተኛ ልጅ የተወገደ እና ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ ካልሆነ (ንዑስ ርዕስ፣ ***የመገለጥ ውሳኔ*** ይመልከቱ) ወይም በልዩ ሁኔታዎች የተባረረ (ንዑስ ርዕስ፣ ***ልዩ ሁኔታዎች*** ይመልከቱ) የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

1. ህጻኑ በአጠቃላይ ትምህርት ስርዐተ ትምህርት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል ለማስቻል፣ በሌላ ቦታ ቢሆንም(በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ሊሆን ይችላል)፣ ትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘቱን መቀጠል፣ እና በልጁ IEP ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሟላት መሻሻል፣ <u>**እና**</u>

2. ተገቢ እንደመሆኑ፣ ተግባራዊ የባህሪ ግምገማ፣ እና እንደገና እንዳይከሰቱ የባህሪ ጥሰትን ለመፍታት የተዘጋጁ፣ የባህሪ ጣልቃገብነት አገልግሎቶችን እና ማሻሻያዎችን መቀበል።

በዚያው የትምህርት ዘመን የአካል ጉዳተኛ ልጅ አሁን ካለበት ቦታ **ለ10 የትምህርት ቀናት** ከተባረረ በኋላ፣ **እና** የአሁኑ መባረር በተከታታይ **ለ10 የትምህርት ቀናት** <u>**ከሆነ**</u> እና መባረሩ የምደባ ለውጥ ካልሆነ (ከታች ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ)፣ <u>**ከዚያ በኋላ**</u> የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ከልጁ መምህራን ቢያንስ ከአንዱ ጋር በመመካከር፣ ህጻኑ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዐተ ትምህርት ውስጥ፣ በሌላ ቦታ ውስጥ ቢሆንም መሳተፉን እንዲቀጥል የሚያስችለውን አስፈላጊ የአገልግሎት መጠን፣ እና በልጁ IEP ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሟላት ለማደግ በሌላ ይወስናሉ።

መባረሩ የምደባ ለውጥ ከሆነ ( ***በማባረር ቅጣት ምክንያት የምደባ ለውጥ*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)፣ የህጻኑ IEP ቡድን ህጻኑ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዐተ ትምህርት ውስጥ፣ በሌላ ቦታ ቢሆንም (ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ሊሆን

ይችላል) መሳተፉን እንዲቀጥል ተገቢውን አገልግሎቶች፣ እና በልጁ IEP ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ለማሟላት ለማደግ ይወስናል።

**<u>የመገለጥ ውሳኔ</u>**

የተማሪ ስነምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ልጅን ምደባ ለመቀየር ማንኛውም አይነት ውሳኔ ከወሰኑበት **በ10 የትምህርት ቀናት** ውስጥ (መባረሩ በተከታታይ **ለ10 የትምህርት ቀናት** ወይም ከዚያ በታች ለሆነ እና የምደባ ለውጥ ካልሆነ በስተቀር ካልሆነ በስተቀር)፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፣ እርስዎ እና ሌሎች የሚመለከታቸው የ IEP ቡድን አባላት (በእርስዎ እና በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እንደተወሰነው) የልጁን IEP፣ ማናቸውንም የአስተማሪ ምልከታዎች እና የሚከተሉትን ለመወሰን በእርስዎ የቀረበ ማንኛውም ተዛማጅ መረጃን ጨምሮ በተማሪው ፋይል ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተዛማጅ መረጃዎች መገምገም አለባችሁ፡-

1. በጥያቄ ውስጥ ያለው ስነ ምግባር የተከሰተው፣ ወይም ቀጥተኛ እና ተጨባጭ ግንኙነት ያለው፡ ከልጁ የአካል ጉዳተኝነት የተያያዘ ምክንያት ከሆነ፣ **<u>ወይም</u>**
2. በጥያቄ ውስጥ ያለው ስነ ምግባር የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የልጁን IEP ያለመተግበሩ ቀጥተኛ ውጤት ከሆነ።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፣ እርስዎ፣ እና ሌሎች የሚመለከታቸው የልጁ የ IEP ቡድን አባላት ከሁለቱ ሁኔታዎች ውስጥ አንዳቸው መሟላታቸውን ከወሰኑ፣ ስነ ምግባሩ የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ እንደሆነ መወሰን አለበት።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፣ እርስዎ እና ሌሎች የሚመለከታቸው የልጁ የ IEP ቡድን አባላት በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህሪ የትምህርት ዲስትሪክቱ የ IEP ያለመተግበሩ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ከወሰኑ፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ እነዚያን ጉድለቶች ለማስተካከል አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለበት።

**ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳተኛነት መገለጫ እንደሆነ መወሰን**

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፣ እርስዎ እና ሌሎች የሚመለከታቸው የIEP ቡድን አባላት ባህሪው የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ መሆኑን ከወሰኑ፣
የ IEP ቡድኑ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ማድረግ አለበት፦

**1.** የምደባ ለውጥ ያስከተለው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ተግባራዊ የባህሪ ግምገማ ካላደረገ እና ለልጁ የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ እስካልተገበረ ድረስ፣ ተግባራዊ የሆነ የባህሪ ግምገማ ማካሄድ፤ ***<u>ወይም</u>***

2. የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ አስቀድሞ ከተዘጋጀ፣ የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድን መገምገም እና እንደአስፈላጊነቱ፣ ባህሪውን ለማስተካከል ማሻሻል።

***ልዩ ሁኔታዎች፦*** *በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ከተገለጸው በስተቀር፣ እርስዎ እና ዲስትሪክቱ የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ማሻሻያ አካል በሆነው የምደባ ለውጥ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጅዎን ተባሮ ወደነበረበት ምደባ መመለስ አለበት።*

### ልዩ ሁኔታዎች

ባህሪው የልጅዎ የአካል ጉዳት መገለጫ ቢሆን ወይም ባይሆንም፣ ልጅዎ የሚከተሉትን ካደረገ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ተማሪውን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ (በልጁ IEP ቡድን ይወሰናል) እስከ 45 የትምህርት ቀናት ድረስ ሊያባርሩት ይችላሉ፦

1. *መሳሪያ* ይዞ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ወደ ትምህርት ቤት ከመጣ ወይም በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ፣ ወይም በ SEA ወይም በትምህርትቤት ዲስትሪክት ስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር ላይ መሳሪያ ከያዘ፤

**2.** በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ግቢዎች፣ ወይም በ SEA ወይም በትምህርትቤት ዲስትሪክት ስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር ላይ እያወቀ *ህገወጥ መድሃኒቶችን* ከያዘ ወይም ከተጠቀመ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጉም ይመልከቱ) ወይም *ቁጥጥር የሚደረግበት እጽ* ከሸጠ ወይም ከጠየቀ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ)፤ ***<u>ወይም</u>***

3. በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ግቢዎች፣ ወይም በ SEA ወይም በትምህርትቤት ዲስትሪክት ስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር ላይ በሌላ ሰው ላይ *ከባድ የአካል ጉዳት* ካደረሰ (ከዚህ በታች ያለውን ትርጉም ይመልከቱ)

### ማብራርያዎች

*ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር* ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት እጽ ህግ (21 U.S.C. 812(c)) በአንቀጽ 202 (ሐ) በ I፣ II፣ III፣ IV፣ ወይም V መርሃግብሮች ስር ተለይቶ የሚታወቅ መድሃኒት ወይም ሌላ እፅ ማለት ነው።

*ህገወጥ መድሃኒት* ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት እፅ ማለት ነው፤ ነገር ግን በህጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ቁጥጥር ስር ጥቅም ላይ የሚውል ወይም በህጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም በዚህ ህግ ወይም በሌላ በማንኛውም የፌደራል ህግ አርቅርቦት ስር ያለ ማንኛውም ባለስልጣን ቁጥጥር የሚደረግለትን እፅ አያካትትም።

*ከባድ የአካል ጉዳት* ትርጓሜ በዩናይትድ ስቴትስ ህግ ርዕስ 18 ክፍል 1365 በአንቀጽ
(3) ንዑስ ክፍል (ሸ) "ከባድ የአካል ጉዳት" የሚለው ቃል የተሰጠው ነው።

*የጦር መሳሪያ* ትርጓሜ በዩናይትድ ስቴትስ ህግ ርዕስ 18 ክፍል 930 በአንቀጽ (2) ስር የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል (ቀ) "አደገኛ መሳሪያ" የሚለው ቃል የተሰጠው ነው።

**ማስታወቂያ**

የተማሪ ስነምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት ለማባረር የምደባ ለውጥ የማድረግ ውሳኔ በሚሰጥበት ቀን፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ስለዚያ ውሳኔ ለእርስዎ ማሳወቅ፣ እና የአሰራር ሂደት ጥበቃዎች ማሳወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል።

## በማባረር ቅጣት ምክንያት የምደባ ለውጥ

አካል ጉዳተኛ ልጅዎን አሁን ካለው የልጅዎ የትምህርት ምደባ ማባረር እንደሚከተሉት ከሆነ **የምደባ ለውጥ** ነው፡-

1. መባረር በተከታታይ ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ ከሆነ፤ ***ወይም***
2. ልጅዎ አንድ የተደጋገመ ሞዴል በሚያቀርብ ተከታታይ የማባረር ሁኔታ ደርሶቦታል፡ ምክንያቱም፡-
    a. በአጠቃላይ በአንድ የትምህርት ዘመን ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ የሆኑ ተከታታይ መባረሮች ደርሰዋል፤
    b. የልጁ ባህሪ ከዚህ ቀደም በነበሩት ተከታታይ መባረሮችን ካስከተሉት ክስተቶች፡
    ከልጁ ባህሪ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል፣
    c. እንደ እያንዳንዱ የመባረር ጊዜ ርዝመት ከእነዚህ ተጨማሪ ምክንያቶች ውስጥ፣ በአጠቃላይ የልጅዎ የተባረረበት ጊዜ፣ እና የተባረረባቸው ጊዜዎች ተቀራራቢነት።

-

የማባረሪያዎች ሞዴል የምደባ ለውጥ የሚወሰነው በእያንዳንዱ ጉዳይ መሰረት ላይ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ከሆነ እና፣ ከተሟገተ፣ ተገቢ በሆነ የችሎት ሂደት እና በፍርድ ሂደቶች ሊገመገም ይችላል።

## የክስተት ቦታ ውሳኔ

የግለሰብ የትምህርት መረሃ ግብር (IEP) ቡድን **የምደባ ለውጥ**፡ ለሚያስከትሉ መባረሮች፣ እና ***ከተጨማሪ ስልጣን*** እና ***ከልዩ ሁኔታዎች*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ላሉ መባረሮች ጊዚያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ይወስናል።

## ይግባኝ

**አጠቃላይ**

በሚከተሉት ካልተስማሙ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት (***ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደቶች*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ) መጠየቅ ይችላሉ፡-

1. በእነዚህ የቅጣት አቅርቦቶች ውስጥ የተደረገ ምደባን በተመለከተ ማንኛውም ውሳኔ፤ ***ወይም***
2. ከላይ የተገለጸው የመገለጥ ውሳኔ።

የትምህርት ዲስትሪክቱ የልጁን ወቅታዊ ምደባ ማስቀጠል በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካመነ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት (ከላይ ይመልከቱ) ሊጠይቅ ይችላል።

### የችሎት መኮንን ስልጣን

***ገለልተኛ የችሎት መኮንን*** ከሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ የችሎት መኮንን ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ማካሄድ እና ውሳኔ መስጠት አለበት። የችሎት መኮንኑ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፦

1. የችሎት መኮንኑ ***በትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን*** በሚለው ርእስ ስር የተገለጹት መስፈርቶች መጣሱን፣ ወይም የልጅዎ ባህሪ የልጁ የአካል ጉዳት መገለጫ እንደሆነ ካወቀ አካል ጉዳተኛ ልጅዎን ወደ ተባረረበት ምደባ ሊመልሰው ይችላል፤ ***<u>ወይም</u>***

2. የችሎት መኮንኑ የልጁን ወቅታዊ ምደባ ማስቀጠል በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ከወሰነ፣ የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ወደ ተገቢው ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ ከ45 የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ እንዲቀየር ሊያዝ ይችላል።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጅዎን ወደ መጀመሪያ ቦታ መመለስ በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ካመነ፣ እነዚህ የችሎት ሂደቶች ሊደገሙ ይችላሉ።

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እንደዚህ አይነት ችሎት ለመጠየቅ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት በሚያስገቡበት ጊዜ፣ ከሚከተሉት በስተቀር ***ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት አሰራሮች*** እና ***በተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ላይ የችሎት ሂደት*** ከሚሉት ርዕሶች ስር የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ ችሎት መካሄድ አለበት፦

1. SEA ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የተፋጠነ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት በመጠየቅ ማዘጋጀት አለበት እንዲሁም የውሳኔ ቀለበት ማስገኘት አለበት፣ ይህም ችሎቱ ከተካሄደበት ቀን በ **<u>20</u>** የትምህርት ቀናት ውስጥ ወይም ከችሎቱ በኋላ ባሉ **<u>10</u>** የትምህርት ቀናት ውስጥ መካሄድ አለበት።

2. እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ስብሰባውን ለመተው በጽሁፍ ካልተስማሙ፣ ወይም ሽምግልና ለመጠቀም ካልተስማሙ በስተቀር፣ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ማስታወቂያ በደረሰው **<u>በሰባት</u>** የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ስብሰባ መካሄድ አለበት። ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት በደረሰው በ**<u>15</u>** የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ሁለቱንም ወገኖች የሚያረካ መፍትሄ እስካላገኘ ድረስ ችሎት ሊቀጥል ይችላል።

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በሌሎች ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ላይ ለሚደረጉ ውሳኔዎች ይግባኝ እንደሚጠይቁት በተመሳሳይ መንገድ ውሳኔውን በተፋጠነ ተገቢ የሆነ የችሎት ሂደት ይግባኝ መጠየቅ ትችላላችሁ (***ይግባኝ*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)።

### <u>ይግባኝ በሚሉበት ጊዜ ምደባ</u>

ከላይ እንደተገለጸው፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ከቅጣት ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ተገቢ የሆነ የቅሬታ ሂደት ሲያስገቡ፣ ልጅዎ (እርስዎ እና ODE ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር) የችሎቱን መኮንን ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ፣ ወይም ***በትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን*** በሚለው ርእስ ስር በቀረበው እና በተገለጸው መሰረት የመባረር ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ፣ የትኛውም ቀድሞ ቢመጣ ፣በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቦታ መቆየት አለበት።

### <u>ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እስከ አሁን ብቁ ላልሆኑ ልጆች የሚደረግ ጥበቃዎች</u>

**አጠቃላይ**

ልጅዎ ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ እንደሆነ ካልተወሰነ እና የተማሪ ስነምግባር ደንብን ከጣሰ፣ ነገር ግን የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የቅጣት እርምጃውን ያስከተለው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት ልጁ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ ካወቀ (ከዚህ በታች እንደተገለጸው)፣ ልጅዎ በዚህ ማሳወቂያ ውስጥ የተገለጹትን ማንኛውንም ጥበቃዎች ሊያረጋግጥ ይችላል።

**የቅጣት ጉዳዮች መሰረታዊ እውቀት**

የቅጣት እርምጃውን ያስከተለው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት የሚከተሉትን ካደረጉ፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ልጅ መሆኑን እንደሚያውቅ ይታመናል፦

1. ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልገው አግባብ ላለው የትምህርት ድርጅት ተቆጣጣሪ ወይም የአስተዳደር ሰራተኞች፣ ወይም ለልጅዎ መምህር ስጋትዎን በጽሁፍ ከገለጹ፤

2. በ IDEA ክፍል ለ መሰረት ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁነትን በተመለከተ ግምገማ ጠይቀዋል፤ ***<u>ወይም</u>***

3. የልጅዎ መምህር ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኞች በልጅዎ ስለታየው የስነምግባር ሁኔታ የተወሰኑ ስጋቶችን ለትምህርት ዲስትሪክቱ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ወይም ለሌሎች የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የበላይ ተቆጣጣሪ ገልጸዋል።

**የተለየ**

የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በሚከተሉት ሁኔታዎች እንደዚህ አይነት እውቀት እንዳለው አይታመንም፡-

1. የልጁን ግምገማ አልፈቀዱም ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ውድቅ አድርገዋል፤ ***ወይም***

2. ልጅዎ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት አካል ጉዳተኛ እንዳልሆኑ ተገምገሞ ተወስኗል።

**የእውቀት መሰረት ከሌለ የሚተገበሩ ሁኔታዎች**

በልጅዎ ላይ የቅጣት እርምጃዎችን ከመውሰዱ በፊት፣ ከላይ ንዑስ ርዕሶች ***ለቅጣት ጉዳዮች የእውቀት መሰረት*** እና ***ልዩነቶች፡*** ስር እንደተገለጹት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ልጅ ስለመሆኑ እውቀት ከሌለው፣ ልጅዎ በንጽጽር ባህሪያት ውስጥ በሚሳተፉ አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ልጆች ላይ በሚተገበሩ የቅጣት እርምጃዎች ሊቀጣ ይችላል።

ይሁን እንጂ፣ ልጅዎ የቅጣት እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ የልጅዎ ግምገማ እንዲደረግ ጥያቄ ከቀረበ፣ ግምገማው በተፋጠነ መልኩ መካሄድ አለበት።

ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ፣ ልጅዎ በትምህርት ቤት ባለስልጣን በተወሰነው የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቆያል፣ ይህም ከትምህርት አገልግሎት ውጪ መታገድ ወይም መባረርን ሊያካትት ይችላል።

ልጁ አካል ጉዳተኛ መሆኑ ከተወሰነ፣ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ከተካሄደው ግምገማ፣ እና በእርስዎ የቀረበውን መረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ከላይ የተገለጹትን የቅጣት መስፈርቶችን ጨምሮ በ IDEA ክፍል ለ መሰረት መስጠት አለበት።

## በህግ አስከባሪ እና የፍትህ ባለስልጣናት የሚደረግ ሪፈራል እና እርምጃ

የ IDEA ክፍል ለ የሚከተሉትን አያደርግም፡-

**1.** አንድ ድርጅት አካል ጉዳተኛ ልጅ የፈጸመውን ወንጀል ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ሪፖርት እንዳያደርግ መከልከል፤ **ወይም**

2. የግዛት ህግ አስከባሪ አካላት እና የፍትህ ባለስልጣናት እና የፌደራል እና የክልል አካል ጉዳተኛ ልጅ ለፈጸመው ወንጀሎች ትግበራን በተመለከተ ሃላፊነታቸውን እንዳይወጡ መከልከል።

**መዝገቦችን ማስተላለፍ**

አንድ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት አካል ጉዳተኛ ልጅ የፈጸመውን ወንጀል ሪፖርት ካደረገ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት፡-

**1.** ድርጅቱ ወንጀሉን ሪፖርት ላደረገባቸው ባለስልጣናት ግምት ውስጥ እንዲገቡ የልጁን የልዩ ትምህርት እና የቅጣት መዛግብት ቅጂዎች መተላለፉን ማረጋገጥ አለበት፤; **እና**

2. በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) በተፈቀደው መጠን የልጁን ልዩ ትምህርት እና የቅጣት መዛግብት ቅጂዎችን ሊያስተላለፍ ይቻላል።

# በህዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ልጆች ወላጆች በአንድ ወገን ምደባ ለማግኘት የሚያስፈልጓቸው መስፈርቶች

## አጠቃላይ

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለልጅዎ ነጻ ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ካቀረበ እና ልጁን በግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ውስጥ ለማስቀመጥ ከመረጡ፣ የ IDEA ክፍል ለ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ላለ አካል ጉዳተኛ ልጅዎ ልዩ ትምህርትን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለትምህርት ወጪ መክፈል አይጠበቅበትም። ይሁን እንጂ፣ የግል ትምህርት ቤት የሚገኝበት የትምህርት ቤት ዲስትሪክት በወላጆቻቸው በግል ትምህርት ቤት የተቀመጡ ልጆችን በሚመለከት በክፍል ለ ከ 34 CFR §§ 300.131 እስከ 300.144 ባሉ አቅርቦቶች መሰረት ትኩረት በሚያስፈልገው ህዝብ ውስጥ ልጅዎን ማካተት አለበት።

**ለግል ትምህርት ቤት ምደባ የክፍያ ማካካሻ**

ልጅዎ ቀደም ሲል በትምህርት ቤት ዲስትሪክት ስር ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ከተቀበለ፣ እና በትምህርት ቤቱ ፈቃድ ወይም ሪፈራል ሳያገኙ ልጅዎን በግል መዋዕለ ህጻናት ትምህርት ቤት፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ከመረጡ፣ ፍርድ ቤቱ ወይም የችሎት መኮንኑ ድርጅቱ ነጻ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ለልጅዎ በወቅቱ እንዳላቀረበ ካወቁ እና የግል ምደባው ተገቢ ከሆነ፣ የችሎቱ መኮንን የምዝገባውን ወጪ እንዲያወራርድ ድርጅቱ ሊያዝ ይችላል። ምደባው በ SEA እና በትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች የሚሰጠውን ትምህርት የግዛት ደረጃዎች ባያሟላ እንኳን የችሎት መኮንን ወይም ፍርድ ቤት ምደባዎ ተገቢ ሆኖ ሊያገኘው ይችላል።

**በማካካሻ ክፍያ ላይ ገደብ**

ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ ላይ የተገለጸው የማካካሻ ወጪ ሊቀነስ ወይም ሊከለከል ይችላል፦

1. ይህም የሚሆንበት፦ (ሀ) ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በተሳተፉበት በጣም የቅርብ ጊዜ የግለሰብ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ ላይ፣ ስጋቶችዎን እና ልጅዎን በህዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤት የማስመዝገብ ፍላጎትዎን ጨምሮ፣የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለልጅዎ ያቀረበውን ምደባ እንደማይቀበሉ ለ IEP ቡድን ካላሳወቁ፤ ወይም (ለ) ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ ቢያንስ 10 የስራ ቀናት በፊት (የስራ ቀን የሚፈጸሙ ማንኛውንም የበአል ቀናት ጨምሮ)፣ ስለዚያ መረጃ ለትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የጽሁፍ ማሳወቂያ ካልሰጡ፤
2. ልጅዎን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጅዎን ለመገምገም ያለውን ፍላጎት (የግምገማው አላማ ተገቢ እና ምክን ያታዊ የሆነውን መግለጫ ጨምሮ) ቀዳሚ የጽሑፍ ማስታወቂያ ከሰጠዎት፣ ነገር ግን ልጁ ለግምገማው እንዲገኝ ካላደረጉ፤ **<u>ወይም</u>**
3. ፍርድ ቤቱ ድርጊትዎ ምክንያታዊ እንዳልሆነ ካወቀ።

ይሁን እንጂ፣ የማካካሻ ክፍያ ወጪው፦

1. የሚከተሉትን ካጋጠመ፡ ማስታወቂያ ባለመስጠት ምክንያት መቀነስ ወይም መከልከል የለበትም፦ (ሀ) ትምህርት ቤቱ ማስታወቂያውን ከመስጠት ከለከለ፤ (ለ) ከዚህ በላይ የተገለጸውን ማስታወቂያ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለብዎ ማሳወቂያ ካልደረሰዎት፤ ወይም (ሐ) ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማክበር በልጅዎ ላይ አካላዊ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ፤ **<u>እና</u>**

2. የሚከተሉትን ካጋጠመ፡ በፍርድ ቤት ወይም የችሎት መኮንን ውሳኔ፣ የሚፈለገውን ማሳወቂያ ባለማቅረብዎ ምክንያት አይቀነስም ወይም አይከለከልም፦ (ሀ) ማንበብ እና መጻፍ ካልቻሉ ወይም በእንግሊዘኛ መጻፍ ካልቻሉ፤ ወይም (ለ) ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች ማክበር በልጅዎ ላይ ከባድ የስሜት ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።